# ያን ቀን በቀራንዮ

እናመሰግናለን ወንድም ኔቪል [“ተባረክ ወንድሜ፡” አለ ወንድም ኔቪልም።—እርታዒ።] እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድም ኔቪል። በጣም አመሰግናለሁ።

2 እንደምን አደራችሁ፡ ወዳጆች። ዛሬ ጠዋት፡ ቃሉን በመሰበክ እና ለታመሙ በመጸለይ ጌታን ለማገልገል፡ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ መገኘት፡ መታደል ነው። ስለዚህ ቀን እጅግ አመሰግናለሁ።

3 እና ልክ እንደገባሁ፡ እየተገረምኩ ነበር። አንድ ወንድም ተነስቶ መጣና “ፈውሰ እንደማይገባው እንደዚያ ለምጻም መሆን አልፈልግም፡” አለኝ። ወንድም ራይት ነው። ጸልዬለት ነበርና፡ ጌታ ሙሉ በሙሉ ፈውሶታል። እርሱም እያለቀሰ፡ እጄን ሊጨብጥ፡ እንዲሁም—ስለፈውሱ፡ ጌታን ማመስገን እንደሚፈልግ—ሊናገር መጣ። ሊያመሰግን መመለስ ፈልጎ ነበር። ሙሉ በሙሉ ጠፍቶለታል። አሁን በፍጹም—ደህንነት ይገኛል። ስለ ምስክርነቶች እናመሰግናለን።

4 እነ ቻርሊ፡ አንተም ወንድም ጀፈሪስ፡ ፍቃዳችሁ ከሆነ፡ ኑ ወደዚህ ውጡ መቀመጫዎች ስላሉ ወሰዳችሁ ተቀመጡ። መቆም አይጠበቅባችሁም፡ መምጣታችሁ እጅግ ያስደሰተናል። ወንድም ዉድ፡ እና እዚያ ጋር ያለው ወንድም፡ ኑ ወደዚህ ውጡ። እናንተም… እዚሁ ትንሹ አግዳሚው ወንበር ላይ፡ ሁለት ቦታ አለ፡ ስለዚህ መቆም አይገባችሁም። ሁለት ቦታዎች፡ አሉ መሰለኝ፡ አዎን፡ መጥታችሁ መቀመጫዎችን ብትይዙ፡ እጅግ ደስታችን ነው።

5 ደስ ብሎን… አንድ ጊዜ፡ “… እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ” እንደተባለ አምናለሁ፡ እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። [አንድ ወንድም “ሁሌም ወደ ሰባኪው መቅረብ እወዳለሁ፡” አለ።—እርታዒ።] አመሰግናለሁ። አመሰግናለሁ፡ አመሰግናለሁ። “ወደ ጌታ ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ፡ ደስ አለኝ።” ወደ ጌታ ቤት መሄድ፡ የክርስቲያን ዕድል እና ደስታ ነው።

6 ዙሪያውን ስመለከት፣ ብዙ ጓደኞቼን በማየቴ፣ ዛሬ ጠዋት፣ በዚህ በጣም ተደስቻለሁ። ከኦሃዮ ወንድም እና እህት ዳውች እዚህ በማየቴ ደስ ብሎኛል። ከኦሃዮ ድረስ ወንድም እና እህት አርምስትሮንግን ከኋላ አይቻቸዋለሁ። ሁላችሁንም፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እና፡ እንደው፡ ዙሪያውን ሳይ፡ ብዙዎችን አያለሁ፣ ሁሉንም ስማቸውን ማስታወስ በጣም ከባድ ነው። እህት ሁቨር፡ ከኬንታኪ፡ ዛሬ ጥዋት፡ አንቺን በማየታችን ደስ ብሎናል። እነ ቻርሊ እና ኔሊ፣ ወንድም ጄፍሪስ እና ቤተሰቡ፣ እና ከከተማ ውጭ የመጣችሁ ብዙዎች።

7 ስለዚህ ዛሬ ጠዋት፡ በጌታ ታላቅ ጊዜን እንጠብቃለን፡ ነፍሳችንን በሚባርክ እና በሚያስፈልገን ነገር እንዲያገለግለን እግዚአብሔር እንዲገናኘን እንጠብቃለን።

8 እና በየቦታው ስመለከት፣ እዚህ ያሉትን ሁሉንም ጓደኞቼን ለመጥራት ብጀምር፣ የተለያዩ ሰሞችን በመጥራት የማለዳው አብዛኛው ጊዜ

ይወስድብኛል። ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቼ፡ ሰዎችን ሁሉ ለማየት ስንገናኝ፡ ጥሩ ስሜት እንዲሰማኝ አድርጎኛል።

9 መንግሥተ ሰማያት ስንደርስስ ምን ይሆን፡ ለታላቁ ዘላለም፡ ለዘለአለማዊ ኅብረት በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ እና፡ ሁላችንም በምንወዳቸው በረከቶች ፊት፡ በዚያ ስንገናኝ ምን ይሆን? በዚያ፡ ሁላችም፡ በአምሳሉ እና በምስሉ እንገኛለን፡ መንፈሱ በእኛ ላይ በመሆኑ፡ ለዘላለም እያመለክነው እና እያገለገልነው፡ ፈጽመን አንደክምም አናረጅም።

10 አስቡት፡ ማድረግ ፈልጋችሁ፡ አስባችሁ የምታደርጉት ነገር፡ በጊዜ ሂደት ግን የማይሰለች ነገር የለም። ቻርሊ፡ በዚህ ረገድ፡ እኔና አንተ ልንሰራ ከምንፈልገው ከማንኛውም ነገር በላይ ሽኮኮ ማደን እንደሆነ አስባለሁ፣ ነገር ግን፡ ታውቀዋለህ፡ በመደረግ ይሰለቻል።

11 በየተራራው ሄጄ ተቆናጥጬ መውጣት—ጉዞ—ማድረግም፡ መውጣትም እወዳለሁ። ከሆነ ጊዜ በኋላ ግን፡ ይሰለቻል፡ ሌላ ነገር ማድረግ ትፈልጋላችሁ።

12 መንዳትም እወዳለሁ። አንዳንድ ጊዜ የድካም ስሜት ይሰማኛል እና እዝላለሁ፣ ነርቮቼ ጫፍ ላይ ይደርሳሉ። መኪናዬ ውስጥ ዘልዬ እወጣና፣ መሪውን ይዤ፡ መንገድ እጀምራለሁ፡ "እንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡" ወይም ሌላ ዝማሬ፡ እየዘመርኩ እሮጣለሁ። መሪውን ይዤ፣ እና እየዘመርኩ፣ እና እግሬን እየረገጥኩ፣ እና እየጮህኩ እሄዳለሁ። ከዛ፡ በቃ፡ ከቆይታ በኋላ፡ ይደክመኛል፡ ከዚያም ወደ ቤት ተመልሼ ሌላ ነገር እጀምራለሁ።

13 ነገር ግን በአዲስቷ መንግሥት እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ ስንደርስ የሚሰለቸን ነገር አይኖርም፡ ዘወትር—በረከት ሆኖ፡ ለዘለአለም ይኖራል። በርግጥ፡ ያኔ፡ እንቀየራለን። አሁን እንዳለን አንሆንም። አሁን ካለንበት አፈጣጠር፡ የተለየ ፍጥረት እንሆናለን። ስለዚህም፡ ደስተኞች እንሆናለን።

14 አንድ አሳብ እያሰብኩ ነበር። ይህ አንቀጽ እዚህ ተናግሬው እንደሆነ እና እናዳልሆነ፡ አላውቅም። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ከወንድም ቻርሊ ጋር፡ ወደ ኬንታኪ ወርጄ ነበር፡ እና እንዲህ አለኝ፣ "ወንድም ብራንሃም፡ በሺው ዓመት፡ እኔ እና አንተ፡ ሽኮኮ እናድናለን ብለህ ታስባለህ? "

እኔም "አይመስለኝም፡ ቻርሊ፡" አልኩት።

15 አለኝም፡- "አሁን፡ በጣም እንወደዋለን፡" "ወደ ሺ ዓመት ከገባን በኋላ—አደን የምንወጣ ይመስልሃል? " አለኝ፤

"አይ፡ በሺው ዓመት ምንም የሚገደል አይኖርም፡" አልኩት።

"እንጃ፡ በጣም ስለምወደው ነው፡" አለኝ።

16 እኔም አልኩት፡- "ቻርሊ፡ እስቲ ከዚህ በፊት አንተ አሳማ ነበርክ፡ ከዛ ግን ከፍ ወዳለው ሰብእና አድገህ፡ ሰው ወደ መሆን ሰብእና አድገሃል ብዬ ባሳምንህ? ወደ ኋላ ተመልሰህ፡ በአሳማ ደስታ ለመደሰት ትሄዳለህን? "

"አልሄድም፡" አለኝ።

17 "እየህ፡ ከአሳማ እጅግ የሚበልጥ ትሆናለህ፡ አሁንም፡ ሰው ሆነሃል፡ ከእንግዲህ ፈጽመህ አሳማ መሆን አትፈልግም፡" አልኩት። ይኸውልህ

አልኩት፦ “ይህን በአሰር ሺ ጊዜ አባዛውና፡ አሁን ካለህበት ሁኔታ ወደፊት ወደሚሆን ማንነትህ ስትቀየር እንዲሁ ነው። ዳግመኛ ሰው መሆን አያምርህም።”

18 ትክክል ነው። የተለየ ነገር ይሆናል። አንድ ቀን ከፍ ወዳለው እንደምንቀየር፡ ማሰቡ ብቻ ደስ ይላል።

19 እንግዲህ፣ አሁን፣ ጌታ ከፈቀደ፣ በሚቀጥለው እሁድ፣ ስለሚሆነው ነገር… ከጓደኛዬ ጋር፡ ወደ ዋዮሚንግ፡ ወይም ወደ አይዶሃ ለመሄድ፡ ከመልካም ወዳጆቼ ጋር፡ ከዚ እወጣለሁ፡ ከወንድም ሚነር አርገንብራይት፡ ወንድም ክላይት ሶንሞር፣ የክርስቲያን ቢዝነስ ሰዎች ጋር።

20 በሚቀጥለው ሳምንት፡ ከሚቀጥለው ሳምንት በኋላ፡ ማለት፡ በ7 ወደ—ዳላስ፡ ቴክሳስ፡ ወደ ቮይስ ኦፍ ሂሊንግ ኮንቬንሽን እገኛለሁ። እኔ የምሰብክበት ምሽት በ7 ነው። እናም ከወንድም አርጋንብራይት እና ከክርስቲያን ቢዝነስ ሰዎች ጋር ወደ አይዳሆ ለመሄድ እመለሳለሁ። ምናልባት ከመሄዳችን በፊት በሚኒያፖሊስ አንድ ምሽት እናድራለን። ከዚያም አንድ የክርስቲያን ቢዝነስ ሰዎች ቁርስ ይኖረናል።

21 ጌታ ቢፈቅድ፡ ቀጣይ እሁድ ማለዳ ወደዚህ ተበርናክል ተመልሼ እመጣለሁ፡ ይህ ግን ጌታ ቢወድ እና ፈቃዱ ቢሆን ብቻ ነው። ጌታ ቢፈቅድ **በነፋስ ውስጥ የሚነፍስ አውሎ ነፋስ**፡ በሚል ርዕስ እሰብካለሁ። ሳምንቱን በሙሉ፡ በልቤ ውስጥ የተመላለሰ ይመስለኛል።

22 በተጨማሪ ባለፈው ጠዋትም፡ በማለዳ፡ ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢ፣ ከእንቅልፌ ነቃሁ እና ይህን ሀሳብ መጣብኝ፣ “ያ ቀን በቀራንዮ።” ዛሬ ጠዋት፡ **ያ ቀን በቀራንዮ፡** በሚል ርዕስ መሰበክ እፈልጋለሁ።

23 እና አሁን ለዚህ ንባብ፡ በመጽሐፍ ቅዱሳችን፡ ከቅዱስ ቃል፡ ከቅዱስ ማቴዎስ፡ 27ተኛው ምዕራፍ እንከፍታለን። ዳራችንን ለማግኘት ከ27ተኛ ቁጥር ጀምረን ከቃሉ ክፍል፡ የተወሰነውን እናነባለን፡ ከዛ ወዲያውኑ እንጀምራለን። እና ከሰብከቱ አገልግሎት በኋላ፡ ለታመሙ ሰዎች ጸሎት ይደረጋል።

24 ኦህ፡ ደግሞ፡ ካለፈው ጊዜ ጀምሮ፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን፡ አዲሱን የአገልግሎቴን አይነት ንድፍ አድርጌአለሁ። ከዚያ ሰብሰባ በኋላ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ያልሰማኋቸው ብዙ ምስክርነቶች ተልከውልኛል።

25 ምንም ያህል ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገር ቢታይም፡ ሰውዬው ማነጋገር የሚያስፈልግበት ነገር ግን ይኖራል። አያችሁ፡ ፈውስ፡ በግለሰቡ እምነት፡ የተመሰረተ መሆን አለበት። እንግዲህ፡ ግለሰቡ ካመነ…

26 እንደው፡ ሰዎች፡ መንፈስ ቅዱስ በጉባኤው ላይ እየተመላለሰ ሲናገር ሲያዩት፡ “**እንዲህ-እንዲህ ሆኗል**። ሰምህም፡ **እከሌ-እና-እከሊት**፡ ትባላለህ። **ከእንደዚህ** አይነት ቦታ የመጣህ ነህ። እንዲህ **አይነት** ነገር ፈጽመሃል። እና **እንዲህ** ይሆናል።” ነገሮች በዚህ መልኩ ሲፈጸሙ ያያሉ!

27 ሆኖም፡ ግለሰቡ፡ በተቀመጠበት፡ ቀና ብሎ አይቶ፦ “ይህ እግዚአብሔር ነው። ፈውሴን እቀበላለሁ፡” ማለት ሲኖርበት።

28 በአንጻሩ፡ ግን፡ ግለሰቡ፦ “እጅህን ጭነህ ጸልይልኝ፡ እና እፈወሳለሁ፡” ይላል። ስለዚህ፡ እዚህ አሜሪካ ውስጥም፡ ያንን ማመን፡ የምንማረው በዚህ መንገድ ነው። በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

29 በአፍሪካ እና በተለያዩ ቦታዎች፡ እንደዚህ አይነት ነገር ሲከሰት፡ ግን፡ ሌላ የተማሩት ነገር ስለሌላቸው፡ ጉባኤው በሙሉ በአንድ ጊዜ ይቀርባሉ፡ ፈውሳቸውን ይቀበላሉ። አያችሁ፡ ስለ ፈውስ እንኳን አልተማሩም። ይሄን ሲያዩ ግን፡ ህያው አምላክ መኖሩን ወድያውኑ ያምናሉ። “እንግዲያውስ ህያው ከሆነ፡ እሱ—ራስ ነው፡ እርሱም—ይፈውሳል።” ዋናው ነገርም ይህ ነው፡ እርሱ ፈዋሽ መሆኑ፡ አስቀድሞ መሰረት ስለተጣለ፡ መሰረት ስለተሰራ፡ ህዝብን ይፈውሳል። ከዚያም መገኘቱ በቤተ ክርስቲያኑ በኩል ሲሰራ ሲያዩ፡ ያን ጊዜ “በቃ፡ የሚያስፈልገን ይህ ነው፡” ይላሉ።

30 እኛ ግን “በሕመምተኞች ላይ እጅ መጫን፡” እና የመሳሰሉትን፡ ተምረናል። በአሜሪካ ውስጥ በደንብ የማይሰራበት ምክንያት ይህ ነው።

31 እንግዲህ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው እሁድ ጥዋት፡ እንዳትረሱ፡ በርግጥ ማስታወቂያውን ወንድም ኔቪል ይናገራል። እና… በ… **በነፍስ ውስጥ ያለ አውሎ ነፋስ።**

32 ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ፡ ከማቴዎስ 27 እንድትከፍቱ፡ ትንሽ ጊዜ ሰጥቻችኋለሁ። ከቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል፡ ከ—ቁጥር 27 ጀምረን እናነባለን። ሲነበብ በደንብ እንስማው።

> በዚያን **ጊዜ የገዢው ወታደሮች ኢየሱስን ወደ ገዢው ግቢ ውስጥ ወሰዱት፡ ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ አከማቹ።**
>
> **ልብሱንም ገፈው፡ ቀይ ልብስ አለበሱት።**
>
> **ከእሾህም አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ፡ በቀኝ እጁም፡ መቃ… አኖሩ፡ በፊቱም ተንበርክከው፡ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፡ ሰላም ለአንተ ይሁን፡ እያሉ፡ ዘበቱበት!**
>
> **ተፉበትም፡ መቃውንም ይዘው፡ ራሱን መቱት።**
>
> **… ከዘበቱበትም በኋላ፡ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፡ ልብሱንም አለበሱት፡ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።**
>
> **ሲወጡም፡ ስምዖን የተባለው፡ የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።**
>
> **ትርጓሜው የራስ ቅል ስፍራ፡ ወደሚሆን ጎልጎታ፡ ወደሚባለው ስፍራ** በደረሱ፡ በወጡ **ጊዜም፡**
>
> **በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤… ቀምሶም፡ ሊጠጣው አልወደደም።**
>
> **ከሰቀሉትም በኋላ፡ ልብሱን ዕጣ** ጥለው **ተካፈሉ፡ ይህም በነቢይ ልብሴን ተካፈሉ፡ በቀሚሴም ላይ** ዕጣ **ተጣጣሉ፡ ተብሎ የተነገረውን ይፈጸም ዘንድ ነው።**
>
> **… በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር፡**

ይህ... ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው የሚል የክሱን ጽሕፈት፡ ከራሱ በላይ አኖሩ።

በዚያን ጊዜ ሁለት ወንበዶች አንዱ በቀኝ፡ አንዱም በግራ፡ ከእርሱ ጋር ተሰቀሉ።

የሚያልፉትም—ራሳቸውን እየነቀነቁ፡ ይሰድቡት ነበርና፡

ቤተ መቅደስን የምታፈርስ ሆይ፡ በሦስት ቀንም የምትሠራው፡ ራስህን አድን፡ ይሉት ነበር። የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፡ ከመስቀል ውረድ አሉት።

እንዲሁም ደግሞ፡ የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሎች ጋር፡ እየዘበቱበት እንዲህ አሉ፡

ሌሎችን አዳነ፡ ራሱን ሊያድን አይችልም። የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ፡ አሁን ከመስቀል ይውረድ፡ እኛም እናምንበታለን።

በእግዚአብሔር ታምኖአልና፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፡ ብሎአልና፡ ከወደደውስ፡ አሁን ያድነው።

ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዶች ደግሞ፡ ያንኑ ነቀፌታ፡ ይነቅፉት ነበር።

ከስድስት ሰዓትም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።

በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ ኤሎሄ፡ ኤሎሄ፡ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ፡ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡ ይህም፡ አምላኬ፡ አምላኬ፡ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው።

በዚያም ከቆሙት ሰዎች፡ ሰምተው፡ ይህስ ኤልያስን ይጠራል፡ አሉ።

ወዲያውም... ከእነርሱ አንዱ ሮጠ፡ ሰፍነግም ይዞ፡ ሆምጣጤ ሞላበት፡ በመቃም አድርጎ፡ እንዲጠጣ ሰጠው።

ሌሎቹ ግን፡ ተው፡ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደ ሆነ እንይ አሉ።

ኢየሱስም፡ ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ፡ ነፍሱን ተወ።

እነሆም፡ የቤተ መቅደስ መጋረጃ፡ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፤ ምድርም ተናወጠች፡ ዓለቶችም ተሰነጠቁ፤

... መቃብሮችም ተከፈቱ፡ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ፡

ከትንሣኤውም በኋላ፡ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና፡ ለብዙዎች ታዩ።

የመቶ አለቃም፡ ከእርሱም ጋር፡ ኢየሱስን የሚጠብቁ፡ ምድር መናወጡንና፡ የሆነውን ነገር አይተው፡ ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ፡ ብለው፡ እጅግ ፈሩ።

34 ጌታ ሆይ፡ አቤቱ አንተ አምላክ እንደ ሆንህ እናውቃለን። እንዲሁም… የተቀደሰው ቅዱስ ቃል ካነበብን በኋላ፣ ባህርይህ አሁንም እንዳልተለወጠ እናያለን። ሁሌም አምላክ ነህና። ኢየሱስም በክፉ እጆች ተይዞ በተቀጠቀጠ ጊዜ፡ በተተፋበት እና በተሳለቁበት በመስቀል ላይም ተሰቅሎ፡ ደም እየደማ፡ በሞተ ጊዜ፡ ምንም አይነት እርዳታ፡ የማያገኝ፡ ይመስል ነበር። “አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውኸኝ?” ብሎ ራሱ፡ እስኪጮኽ ድረስ፡ ረዳት፡ ከየትም የሚያገኝ አይመስልም ነበር፡

35 አንተ ግን፡ ምንም ነገር ማድረግ በማይቻልበት ቅጽበት ትሰራለህ። ጌታ ሆይ፡ መሻገር የማንችላቸው ወንዞች ከገጠሙን፡ መውጣት የማንችላቸው ተራሮች ከተጋረጡብን፡ እግዚአብሔር ሌሎች የማይችሉትን በመቻል እስፔሻላይዝ ያደረገ መሆንኑን፡ እናውቅ ዘንድ ተሰጠን።

36 በቀራንዮ ላይ የዚያን ቀን የነበረውን ምክንያት አንተ ታውቃለህና፡ በሥራህ ላይ፣ ስፔሻሊስት ነህ። አንተ፡ ፍጻሜ የሌለው፡ አምላክ ስለሆንክ፣ ይህች ሰዓት እንድትመጣ ታውቃለህ። በተፈጸመ ጊዜ ግን ያን ጊዜ አንተ አምላክ እንደሆንህ አሳይተሃል። ገዢ ማን እንደነበር አሳይተሃል። ምድርን አናወጠህ፡ ምድር ውስጥ የተኙ ቅዱሳን ሁሉ አወጣህ። አምላክ መሆንህን አሳይተህ እንደ ሌሊት ጨለማ በቀን ፀሐይን አጨለምክ። ይህን ያህል ጊዜ ግን ዝም ያልክ ይመስላል።

37 እንግዲያውስ ከዚህ ተነስተን፡ ወደዚህ ማጠቃለያ ሐሳብ፡ እንደርሳለን፡ በእግዚአብሔር እጅ እየተመራን፡ በመንፈስ እስከተመላለስን ድረስ፣ ምንም ዓይነት ስህተት ቢመስልም፣ ቀራንዮን በመጋፈጥ ላይ ነን፡ እግዚአብሔር በትክክለኛው ሰዓት፡ በትክክለኛው ጊዜ ይናገራል።

38 አሁንም፡ እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ለኃጢአታችን እና ለበደላችን ይቅርታን እንለምንሃለን። መንፈስህን እንዲመራን እንለምናለን። ርግብ በጉን እንደምትመራው፡ ምራን። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በመልካም እንደሚሰራ በማወቅ፣ እና መልካም እንደሚሆን እውቀን፡ ለሚደርስብን ሁሉ ታዛዦች እንሁን።

39 በጉባኤው ዛሬ ከእኛ ጋር ሁን። ለመዳን የተዘጋጁትን፡ እና መዳን የሚፈልጉትን እንድታድናቸው እንጸልያለን። እነዚህን የሚፈልጉት፡ የዘላለም ሕይወትን ሙላ። የታመሙትን እና የተጎዱትን፡ ፈውስ ፈልገው የመጡትን፡ እንድትፈውሳቸው እንጸልያለን። ለእርሱም እናመሰግንሃለን። በልጅህ፡ በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

40 አሁን፣ ዛሬ ጠዋት በንግግር ወቅት፣ ልናገር ወደመረጥኩት ርዕስ ትኩረት እንድትሰጡ እንፈልጋለን፡ **ያን ቀን በቀራንዮ**።

41 ምናልባት ይህ በአርብ ስቅለት የሚደረግ ስለሆነ፡ አለጊዜው ሊመስል ይችላል። ቀራንዮ ግን በየቀኑ መታሰብ አለበት። ስለሱ ብዙ ሰምተናል፡ ብዙም አንብበናል። ከጥንት ጀምረው ሰባኪዎች በዚህ ርዕስ ላይ ሰብከዋል። ዘማሪዎችም፡ በዘመናት ሁሉ ዘምረውታል። ከመፈጸሙ ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት፡ ነቢያት ተንብየውታል። የዚህ ዘመን ነቢያት ደግሞ ያኔ የተፈጸመበትን ያመለክታሉ። በጣም የተለየ ቀን ነው! እግዚአብሔር በምድር ላይ ኀህ

እንዲቀድ ካደረጋቸው ቀናት ሁሉ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ቀናት ውስጥ አንዱ ነው።

42 ስለዚህ ቀራኒዮ፣ ለሰዎች ልጆች የተለየ ቀን ከሆነ፣ ወደ ኋላ ተመልሰን እንድንመረምር፣ ለእኛ ምን ማለት እንደሆነ ብናየው ጥሩ ይመስለኛል። እርግጠኛ ነኝ፣ በዚህ በምንኖርበት እንጥፍጣፊ ሰአት፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ልናውቀው የሚያስፈልገን ሁሉ ለማወቅ እየጓጓን፣ ነንና። ማግኘት የቻልነውን ሁሉ፣ ለእኛ ያለውን ለማየት፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን፣ እና እሱ ለእኛ ቃል የገባውን ለማየት፣ ለመማር ተሰብሰበናል። ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንመጣውም ለዚህ ነው። ሰባኪውም የሚሰብከው፣ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያጠናው እና የሚያሰላስለው፣ ለእኛም ማነሳሻን የሚፈልገው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋይ ስለሆነ ነው። እና የሆነ ነገር ለማግኘት... እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚናገረውን፣ የሚጠቅማቸውን ነገር ለማግኘት ይሞክራል። ምናልባት፣ ምናልባት፣ በኃጢአታቸው ይወቅሷቸዋል፣ ነገር ግን ኃጢአታቸውን ትተው፣ ጌታን ለማገልገል እንዲነሡ እነርሱን ለማሳደግ ይጠቅሟቸዋል። አገልጋዮችም እነዚህን ነገሮች መፈለግ አለባቸው።

43 እና ይህ ቀን፣ በጣም አስፈላጊ፣ ከታላላቅ ቀናት አንዱ በመሆኑ፣ ያ ቀን ለእኛ ትርጉም ያላቸውን ሶስት የተለያዩ ነገሮችን እንመለከትበታለን። በመቶዎች የሚቆጠሩ ማውጣት እንችላለን። ቢሆንም ግን፣ ለዛሬ ጠዋት፣ ሶስት የተለያዩ፣ ጠቃሚ ነገሮችን መርጫለሁ ቀራኒዮ ለእኛ ምን እንደሆነ፣ ለሚቀጥሉት ጥቂት ጊዜያት፣ ማየት እንፈልጋለን። እናም የተገኙትን ኃጢአተኞች ሁሉ እንዲኮንን፣ ቅዱሳንን ሁሉ በጉልበታቸው እንዲወድቁ፣ የታመመ ሰው ሁሉ፣ እምነቱን ወደ እግዚአብሔር እንዲያሳድግ፣ እና ተፈውሶ እንዲሄድ፣ ኃጢአተኛ ሁሉ፣ ድኖ፣ ከዳተኛው ሁሉ ተመልሶ፣ በራሱ ያፍር ዘንድ፣ ቅዱሳን ሁሉ፣ እንዲደሰቱ፣ አዲስ ተስፋን እና አዲስ አቋም እንዲይዙ እጸልያለሁ።

44 ቀራኒዮ ለእኛ እና ለአለም፣ አንዱ ትልቁ ጠቃሚ ነገሩ፣ የኃጢያት ጥያቄን፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፣ መፍታቱ ነው። ሰው በኃጢአት ጥፋት ተገኝቶ ነበርና። ኃጢአት ደግሞ ማንም ሊከፍለው የማይችለው ዕዳ ነው። ዕዳውን መክፈል የሚችል ሰው እስከማይገኝ ድረስ ታላቅ ዕዳ ነበር። በእውነት እግዚአብሔር የመደበው እንደነበረ አምናለሁ፣ ይህም ዕዳው ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ፣ ከእርሱ በቀር፣ ሌላ የሚከፍል እንዳይገኝ ነው። እንግዲህ፣ የኃጢአት ዕዳ ሞት ነበር። እኛ ሁላችን በኃጢአት ተወልደን፣ በዓመጻ ተፈጠርን፣ ውሸት እየተናገርን፣ ወደ ዓለም መጥተናል። ስለዚህ ማንኛችንም ብንሆን ብቁዎች አልነበርንም፣ ወይም፣ በምድር ላይ የበቃ ሰው ማግኘት አልቻሉም።

45 ኃጢአትም በምድር ላይ አልጀመረም። ኃጢአት የጀመረው በሰማይ ነው። ሉሲ-... ፈር... ሉሲፈር፣ ዲያብሎስ፣ ምድርን ከመምታቱ በፊት፣ ባለመታዘዙ የተወገዘ ፍጡር ነበር። ሐጥያት የጀመረው፣ እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች እንዲኖሩበት እንደደነገገው በተመሳሳይ ድንጋጌ መሰረት፣ መላእክትን እና ሌሎችን ሁሉ፣ ባደረገበት በሰማይ ነው፣ እውቀት፣ የእውቀት ዛፍ፣ የህይወት ዛፍ እና የእውቀት ዛፍ፣ የሰው ልጅ ምርጫውን የሚወስድበት። ሉሲፈርም ምርጫውን እንዲያደርግ፣ የበላይነት በተሰጠው ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ከነበረው ነገር የተሻለ ነገር ፈለገ። የችግሩ መጀመርያም ይህ ነው።

46 ለኃጢአትም መሰፈርት ነበረው። መሰፈርቱም ሞት ነበር። ሞት ዕዳው ነበር። ይህ ማለት፡ ስለዚህ ጉዳይ፡ በዝርዝር ልንናገር እንችላለን፡ ምክንያቱም አንድ ሞት ብቻ አለ ብዬ አላምንም። አንድ ሕይወት አለ። የዘላለም ሕይወት ያለው ሰው ፈጽሞ ሊሞት እንደማይችል አምናለው። ሐጢያትን የምትሰራ ነፍስ ፍጹም ጠፊ እንደሆነች አምናለሁ፡ መጽሀፍ ሲናገርም "ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ፡ በእርግጥ ትሞታለች፡" ይላልና። ሰው አይልም፦ "ኃጢአት የምትሠራ **ነፍስ**።" ስለዚህ፡ ሰይጣንም ፈጽሞ ይጠፋ ዘንድ፡ መሞት አለበት። ሰይጣን ይድናል ከሚሉት ዓለም አቀፋውያን አቀንቃኞች ጋር አልስማማም! ኃጢአት ሠርቷል፡ የኃጢአት ጀማሪ እርሱ ነው። ነፍሱም ኃጢአት ሠራች፡ መንፈስም ነበረ። ያ መንፈስም፡ ምንም እስከማይገኝ ድረስ ፈጽሞ ይጠፋል።

47 በመጀመርያ፡ ሐጥያት ከሰማይ እንደ ሰሰ ጥቁር ሸማ ወርዶ፡ ምድርን በመታ ጊዜ፡ ምድርን ሸባ አድርጓታል። የምድር ፍጥረትን ሁሉ፡ እና የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሁሉ፡ በባርነት፡ ጣላቸው። ሰው በሞት፡ በበሽታ፡ በችግር፡ በሐዘን ባርነት ውስጥ ነበር። ተፈጥሮም ሁሉ ከእርሱ ጋር ወደቀ። ኃጢአት በእርግጥ ምድርን ሸባ ያደረገ ማደንዘዣ ነበር። የምድር ፍጥረት ሁሉ ለሱ ባርያ ነበርና፡ እኛም ተሰፋ ቢሶች ሆነን፡ ተቀምጠን ነበርን። በምድር ላይ የተወለደ ሁሉ ለእርሱ ባርያ ሆኖ ነበር።

48 ስለዚህ ኃጢአት ከሌለበት ቦታ፡ አንድ መምጣት ነበረበት። ከምድር ሊመጣ አይችልም። አንዳችን ሌላውን መዋጀት አልቻልንም። ከሌላ መምጣት ነበረበት።

49 ስለዚህ፡ ሰው ከአምላኩ መለየቱን ሲያውቅ፡ ተቅበዝባዥ ሆነ። አነቡ። አለቀሱ። ደከሙ። ፈጣሪዋና ሰሪዋ አምላክ የሆነላትን ከተማ እየፈለጉ፡ በተራሮችና፡ በምድረ በዳዎች፡ ዞሩ። ምክንያቱ፡ በእግዚአብሔር ፊት ተመልሶ ከመጣ፡ ከእርሱ ጋር መነጋገር እንደሚችል ያውቃልና። የሚመለሰበት መንገድ አልነበረውም። ጠፋ። በየትኛው መንገድ መመለሰ እንዳለበት አያውቅም፡ ስለዚህ ተጉዞ፡ ወደዚያ ቦታ የሚመለሰበትን ቦታ ለማግኘት እየሞከረ፡ እየተንከራተተ ወጣ። ከውስጥ ከማንነቱ—ፍጹም ከነበረው ሰፍራ ወድቀሃል ብሎ ነግሮታል። ዛሬ ጠዋት፡ በዚህ በሚታዩ ታዳሚዎች፡ ወይም በመላው ዓለም በሚሰራጨው፡ በመግነጢሳዊ ቴፕ ባሉ ታዳሚዎች መካከል፡ እዚም ካሉ ይሁን፡ ወይም የትም፡ ያንን ፍጽምና የማይፈልግ ሰው የለም።

50 የአገልግሎት ክፍያዎችን ከከፈላችሁ በኋላ፡ "እርፋለሁ፡" ብላችሁ ታሰባላችሁ። የአገልግሎት ክፍያዎቻችሁን ከከፈላችሁ በኋላ ግን፡ ከቤተሰብ አባል አንዱ ይታመማል። ህመሙ ካለፈ በኋላ፡ ተጨማሪ የአገልግሎት ክፍያ ይመጣባችኋል። በመጀመርያ የምታሰተውሉት፡ ጽጉራችሁ መሸበት እንደጀመረው ነው፡ ከዚያ ወጣት መሆን ትፈልጋላችሁ። በዚያ የሐጢያት ሞገድ ምክንያት፡ ሁል ጊዜ ያለማቋረጥ፡ አንድ ነገር ይከሰታል። ነገር ግን በልባችሁ ውስጥ፡ ያን ስለምትፈልጉ፡ የሆነ ቦታ ፍፁምነት እንዳለ ያሳያል። የሆነ ቦታ ላይ፡ የሆነ ነገር አለ።

51 ለዚህ ነው፡ ብዙ ጊዜ፡ ዛሬ፡ ኃጢአተኛው አሁንም እየተንከራተተ ያለው። አንዲት ቆንጆ ወጣት ልጃገረድ፡ ተወዳጅ ለመሆን፡ ፀጉሯን ትቆርጣለች፡ ቆንጆ እንድትመስል ፊቷን ቀለም ትቀባለች፡ የሰውነቷን ቅርጽ የሚያሳዩ ልብሶችን

ትለብሳለች። ወደ ራሷ የሚመልሳት ነገር ለማግኘት የምትሞክርበት ብቸኛው ሁኔታ በመፈለግ የምታገኘው ብቸኛው ነገር፡ ይህ ነውና፡ ይህም ወንዶች እንዲያፏጬባት፡ እንዲጠቁሙባት፡ እና እንዲያሽኮረሙሟት ስታደርጋቸው ብቻ ነው። ወጣቱ በሴቲቱ ላይ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፡ እራሱን ለእሷ ማራኪ ለማድረግ ይሞክራል። ጎረቤቶች ቤት ይሠራሉ፡ ምክንያቱም ከጎረቤቱ ቤት ትንሽ የተሻለ እንዲመስልለት፡ በተወሰነ መንገድ ያስተካክላሉ። ሁል ጊዜ፡ የሆነ ነገር እየፈለግን ነው፡ የሆነ ነገር ግን ወደ ላይ ትንሽ መሄዱን ይቀጥላል። ወጣቷ ሴት ከእሷ የበለጠች ተወዳጅ የሆነች ሌላ ወጣት ሴት ትገጥማታለች። ጎረቤቱ ከእሱ የተሻለ የሚመስል ቤት ይገጥመዋል። ሴትየዋ ከእሷ በተሻለ መልኩ፡ የለበሰች የሚመስል ሌላ ሴት ትገጥማታለች።

52 በውስጣችን የሆነ ነገር፡ የሆነ ነገር እየፈለገ ያለው፡ እንደጠፋን ማሳያ ነው። ወደዚያ እርካታ የሚያመጣን የውስጣችን ረሃብ የሚሞላ፡ አንድ ነገር ማግኘት እንፈልጋለን፡ ይሁን እንጂ ማግኘት የምንችል አይመስለኝም። የሰው ልጆች በዘመናት ሆሉ ሞክሮውታል። አለቀሱ። አነቡ። ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ፣ ቢሆንም አላገኙትም፡ በዓለም ውስጥ እየተንከራተቱ ይገኛሉ።

53 በመጨረሻም፡ አንድ ቀን ግን፡ በቀራንዮ ላይ፡ አንድ ሰው ከአርያም ወረደ። ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ፡ ከአርያም የመጣ፡ አንድ ነበረ፡ እርሱ ቀራንዮን አበጀ። ይህም ዋጋ የተከፈለበት፡ እና የኃጢአት ጥያቄ ለዘላለም የተፈታበት ቀን ነው። ለእኛም ለራሃብ እና ለጥማታችን መንገድ ከፈተልን። የእርካታ ሰፍራ አመጣልን። ቀራንዮን ጎብኝቶ፡ እንዴት እንደነበረ አይቶ፣ ሳይቀየር የቀረ ማንም ሰው የለም። ወደዚያ ቦታ ሲደርስ፡ የሚፈልገው ወይም የሚናፍቀው ነገር ሁሉ፡ ያገኛል።

54 ዓለምን ያናወጠ፡ በጣም ልዩ ቀን፡ እና የተለየ ነገር ያለው ቀን ነው። ዓለም ከዚህ በፊት አይታው የማታውቅ ነውጥ፡ ያናወጠ ቀን ነው። ኢየሱስ በቀራንዮ ሞቶ የኃጢያትን ጥያቄ ሲከፍል፡ ይህ ኃጢአተኛው ዓለም ጨለማ ወርሶት ነበር። በእኩለ ቀን ላይ ፀሐይ ተሰወረች፡ የምትሆነው አሳጣት። ድንጋዮቹም ተንቀጠቀጡ፡ ተራሮችም ተሰነጠቁ፡ ሙታኖች ከመቃብር ወጡ።

55 ይህስ ምን አደረገ? እግዚአብሔር ሰይጣን የተባለውን እንስሳ፡ ለዘላለም፡ አቆሰለው። በቀራንዮ ላይ፡ ባዶ አደረገው። አሁንም ብርሃን ለሰው ልጆች ስለመጣ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የበለጠ ጨካኝ ሆኗል። ይህ የቆሰለው እንስሳ ጨካኝ እንደሆነ ማንም ሰው ቢያውቀውም፡ ወገቡ ተሰብሮ እየተጎተተ ነው። ስለዚህ፡ ሰይጣን፡ በቀራንዮ ላይ ተዘርሯል። መዘረሩን ምድርም መሰክራለች።

56 እስከ ዛሬ የተከፈለው ትልቁ ዋጋ፡ እና የከፈለው ብቸኛው አካል፡ መጣና በቀራንዮ ሰራው። ትልቅ ዋጋ የተከፈለበት ቦታ ያ ነው። ከነገሮቹ አንዱ ያ ነው። እግዚአብሔር ፈለገ። አንድም ሰው ብቁ አልነበረም። አንድም ሰው አልቻለም። አንድም ሰው ማድረግ አልቻለም። እግዚአብሔርም ራሱ መጥቶ፡ ሰው ሆነ፡ ሰው በሚፈተንበት ሁሉ፡ ሰው ሆኖ ተገኘ፡ በቀራንዮም ተሰቀለ። በዚያም ሰይጣን፡ አይችለውም ብሎ ባሰበው ጊዜ፡ ይሄን ማለፍ አይችልም ባለው ጊዜ፡ የጌተሰማኒ ፈተናዎችን ሁሉ ጥሶ አንድም ሰው መቋቋም ያልቻለውን አልፎ ሄደ። ልክ እንደ ሰው ሁሉ በዚያ አለፈ፡ ነገር ግን ዋጋ ከፈለ።

57 ምድርን ጨለማ ያደረጋት ነገርም ያ ነበር። ለቀዶ ጥገና እንደሚደረግ፡ ማደንዘዣ ነበረ። ዶክተር ለአንድ ሰው ማደንዘዣ ሲሰጥ፡ ምንም ነገር ከመሰራቱ በፊት፡ ራሱን እንዲስት ያደርገዋል። እግዚአብሔርም—ለቤተክርስቲያን ቀዶ ጥገና ባደረገላት ጊዜ፣ አለም ማደንዘዣ ተወጋች፡ ተፈጥሮ መናወጥ ነበረበት። ምንም አያስገርምም! እግዚአብሔር፡ በሰው ስጋ፡ ሞቷልና። ዓለም ስትናፍቀው የነበረው ሰዓት ነበር፡ ብዙዎቹ ግን አላወቁትም።

58 ልክ እንደ ዛሬው፡ ብዙዎች እነዚህን ነገሮች ሲናፍቁ ነበር፡ ነገር ግን አላወቁትም። መውጫ መንገዱ አያውቁትም። አሁንም መውጫውን ፍለጋ፡ ተድላዎችን እና የአለምን ነገሮች እየተመኙ ነው።

59 ቀኒቱን የሚጠቁሙ ብዙ የምልክት ምስሶዎች፡ ብዙ ታላላቅ ግምቶች ነበሩ። በበግ፡ በወይፈን፡ በዋኖሶች፡ እና በእነዚህ ነገሮች ጥላ ሁሉ ታይቶ ነበር፡ ይህ ሁሉ ግን ሊሰብረው አልቻለም ነበር። ሰይጣን ምድርን የያዘበት፡ የሞት መውጊያውን መሰበር አልተቻላቸውም።

60 በአንድ ወቅት እንደሚነድ ዲን፡ ወደ-ላይና-ታች በምድር የተመላለሰባቸው ዓለቶች! ሉሲፈር የንጋት ልጅ ነበርና፡ የሚነድ እሳተ ገሞራ ሆኖ በምድር ላይ ተመላልሶ ነበርና። ኢየሱስ በቀራንዮ ሲሞት፡ ቀዝቅዘው የነበሩ እነዚያ ዓለቶች፡ ምድርን ሰንጥቀው ወጡ።

61 በተከፈለው ዋጋ፡ የሰይጣን እስራት ተበጣጥሷል። ሰው ወደሚፈልገው የሚመለሰበትን መንገድ እግዚአብሔር በሰው እጅ ላይ አኖረ። ማልቀስም አይገባውም። ይህም፡ የሰይጣንን ወገብ፡ በኃጢአት ምክንያት የመጣ፡ የበሽታን ወገብ፡ ቀራንዮ ላይ መትቶ ከሰበረው በኋላ ነው! ይህም በምድር ያሉ፡ ሟች ፍጥረታት በሙሉ፡ ኃጢአታቸውን በማስወገድ፡ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ዳግም ይመልሳቸዋል። ሃሌ ሉያ! ኃጢአታችን ተሰርዮልናል። ከዚህ በኋላ ሰይጣን እኛን ከእግዚአብሔር ሊያጠፋን አይችልም።

62 አውራ ጎዳናው ተሰርቷል። ቴሌፎን ተዘርግቷል። ሰውን ሁሉ የተዘረጋውን መሰመር መጠቀም የሚችልበትን፡ ወደ ክብር የተዘረጋ መሰመር አለ። ሰው ኃጢአት ቢሰራ፡ በማዕከላዊው መሰመር ውስጥ ያገናኘዋል። ኃጢአቱ ይቅርታን ማግኘት ይችላል። ይህ ብቻ አይደለም፡ ኃጢአት ዋጋ ተከፍሎበታል። ኦ! “ብቁ አይደለሁም፡” ማለት የለብህም። እርግጥ ነው፡ አይደለህም፡ በፍጹም ልትሆን አትችልም። ግን ብቁ የሆነው እርሱ ሰፍራህን ተክቷል። ነፃ ነህ። ከእንግዲህ መንከራተት የለብህም። እዚህ ምድር ላይ ተድላ-ፈላጊ ሰው መሆን አያስፈልግህም።

ከአማኑኤል ደም ሰር የሚቀዳ፡
የደም ምንጭ አለ፡
ኃጢአተኞች ከጅረቱ በታች ሲወድቁ፡
የኩነኔአቸው እድፈት ይለቃል።

63 መጥፋት አይገባችሁም። አውራ ጎዳናው አለ፡ መንገድም አለ፡ እሱም የቅድስና መንገድ ይባላል። እርኩሰትን የሚሰሩ አይለፉበትም። ምክንያቱ፡ አስቀድሞ፡ በምንጩ በኩል አልፎ፡ ወደ አውራ ጎዳናው ገብቷል።

64 የሰይጣንንም ኃይል ሰብሯል። በዚህ ምድር፡ በእስር ቤቶች ውስጥ፡ ተዘግቶባቸው፡ ከሞትኩ በኋላ ሞት ምን ያደርገኛ ይሆን ብለው፡ በፍርሃት

ለነበሩ ሰዎች ሁሉ፡ የገሃነምን ደጆች ከፈተላቸው። በቀራንዮ ላይ፣ እነዚያን የእስር ቤት መዝጊያዎችን ከፈተ፣ ምርኮኞችን ሁሉ ነጻ አወጣ። ከአሁን በኋላ በኃጢአት መሰበር ቀረ። ከእንግዲህ ወዲህ ብልቶቻችሁን የአመጻ መሳርያ አይሁን፡ መጠጣት፡ ማጨስ፡ ቁማር፡ ውሸታምነት ይቅር። ሐቀኛ፡ ፍትሐዊ፡ እና ቅን መሆን ትችላላችሁ። መሰመሩን፡ ማለት በጥንቱ አምባ ላይ የተዘረጋ የህይወት-መሰመር ስለያዛችሁ፡ ሰይጣን ምንም ሊያደርጋችሁ አይችልም። ከእርሱ ሊያናውጣችሁ ማንም አይችልም። የትኛውም ወጀብ አያናውጣችሁም። ማንም አይችልም፡ ሞት ራሱ፡ በክርሰቶስ ኢየሱስ ካለው የእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም። ቀራንዮ ማለት ያ ነው።

65 በባርነት ውስጥ የኖረ ህዝብ ከእስራት ተፈታ። በሞት ፍርሃት የኖሩ ሁሉ ከእንግዲህ ሞትን አይፈሩም። ሰሪዋ፡ እና ፈጣሪዋ፡ እግዚአብሔር የሆነች ከተማ የሚፈልግ ሰው፡ ፊቱ ወደ ሰማይ አሻቅቦ፡ እግሮቹ በአውራ ጎዳናው ላይ መርገጥ ይችላል፡ ነጻ ሆኗልና። ሃሌ ሉያ! ቤዛነት አግኝቷልና። ትክክል ሁኑ አትሁኑ የሚያውቅበት መንገድ ሰላለው፡ ከእንግዲህ መንከራተት አያስፈልገውም። እግዚአብሔር ሕይወት ሰጠን። በዛች ቀን በቀራንዮ ላይ ዋጋ ከፍሏልና። ኃጢአታችን ተወግዷል። ያን ሁሉ ሰናይ ገጣሚው እንዲህ ሲል መጻፉ አያስገርምም፡-

> በሚሰነጠቁ ድንጋዮች እና በጠቆሩ ሰማያት መኃል፡
> አንገቱን ደፍቶ አዳኜ ሞተ፡
> የተከፈተው መጋረጃ መንገዱን ገለጠ
> ለገነት ደሰታ እና ማለቂያ ለሌለው ቀን።

66 አብርሃም ከአሁን በኋላ ከተማ እየፈለገ፡ በአገሪቱ፡ አይንከራተት። ኃጢአተኛው እድናለሁ አልድንም ብሎ አይጨነቅ። የታመመው ሰው እፈወሳለሁ ወይስ አልፈወስም አይበል። ያን ቀን በቀራንዮ፡ በከፈተው መጋረጃ፡ ወደ ፍጹም ድል የሚያደርሰ መንገድ ገልጧል። በእነዚህ ሁሉ ላይ በድል እንድንኖር እግዚአብሔር እንድናምን ብቻ ጠየቀን፡ የመንፈሱን ኃይል ሰጠን። ያን ቀን በቀራንዮ እንዲህ ሆነ። እንደዚያ ያለ ቀን አልነበረም። መቼም እንደሱ አይነት አይኖርም። ከአሁን በኋላ አሰፈላጊ አይደለም። ዋጋው ተከፍሏል፡ ተቤዥቶናል። እግዚአብሔር ይመሰገን! ተቤዥቶናል። ከአሁን በኋላ መንከራተት አያስፈልግም። መገመት አያስፈልግም። ሁሉም ተወስዶላችኋል። ጨርቁን መጋረጃውን ወደ ኋላ ጎተተው፣ እኛም በአውራ ጎዳናው ላይ ገብተናል፣ ይህም እንደገና እንድንቅበዘበዝ ሳይሆን፡ አምነን በጽድቅ እንድንጓዝ ነው። በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር መገኘት እንሄዳለን።

67 አብርሃምም፡ ሌሎችም፡ ከተማይቱን ሲፈልጉ፡ ከሌላ አገር መሆናቸውን፡ አውቀው ነበር። የሆነ ነገር ተከሰተ። ሸባ በሆነች ምድር ይኖሩ ነበር። የመሬት መንቀጥቀጥ መጣ። አውሎ ነፋሶች መጡ። ጦርነቶች እና ግድያዎች! ተኩላና በጉ እርስ በርሳቸው ተበላሉ፡ ተኩላው በጉን፡ አንበሳም በሬውን በላው። ችግር አለ። ትክክል አይመስልም። የሆነ ችግር እንዳለ ያውቅ ነበር። ሰዎች ሰዎችን ወንድሞች ወንድማቸውን ይገድላሉ፡ አባት ልጁን ይገድላል፡ ልጅ አባቱን ይገድላል። የሆነ ችግር አለ። አርጅቷል። ሊሞት ተቃርቧል። ደርቋል። በሽተኛ ሆኗል። እሰራት ላይ ነው። ዛፎቹ ያድጋሉ፡ የማይሞቱ ግን አይደሉም። ይሞታሉ። ተራሮች ይለወጣሉ። ባሕሮች ይደርቃሉ። ውኃው ተመርዟል። የሆነ ችግር አለ።

እርሱ ግን፡ ይህን የማይሆንባትን ከተማ ፈለገ። ይህን ሁሉ ትክክል አድርጎ ወደ ሰራው ከደረሰ፡ ከእርሱ ጋር እንደሚነጋገር፡ ያውቃልና።

68 ኦህ፣ ኃጢአተኛ ሆይ፣ አሁን መንገዱን እንዳገኘህ ማወቅህ፡ ዛሬ ጠዋት እንዴት ያለ መታደል ነው። ያን ቀን በቀራንዮ መንገዱን ከፈተ። አባቶች ሁሉ ፈልገዋታል ጠብቀዋታል፡ ቀራንዮ ግን፡ በነጻ ሰጥታችኋለች። እንዴት ትክዱታላችሁ? የሐይማኖት ተቋምን ለመቀላቀል፡ እንዴት ትክዱታላችሁ? በዓለምን ደስታዎች፡ በማይረባ ነገር እሱን ለመተካት፡ እንዴት ትክዱታላችሁ? ለምን አትቀበሉትም? የመጋረጃው መከፈት፡ ሰውን ምንም አይነት የኃጢአት ሽታ ሳይኖርበት፡ ወደ እግዚአብሄር ህልውና ያቀርበዋል። ወደሚፈልገውም ነገር በፊቱ መንገድ ያዘጋጅለታል፡ ሰማይ፣ ክብር፣ ሰላም፣ የዘላለም ሕይወት፣ ሁሉም በፊቱ ያደርግለታል።

69 ያቺ ቀን—ለሰይጣን ኃይል የሞቱ ምት ነች። ሁሉንም ነገር አበቃ።

70 ከሩቅ አየዋለሁ፡ እርሱ ከወጣበት ከመጀመርያው ጥላ ጀምሮ፡ የኤደኑ ጠቦት እርሱ ነበር።

71 አቤል፡ በእምነት፡ ከቃየን የሚበልጥ መስዋዕትን ለእግዚአብሔር ባቀረበ ጊዜ፡ የወይን አረግ—በጠቦቱ አንገት ላይ አሰሮ፡ ወደ አለቱ ሳይጎትተው አይቀርም። የሚያርድበት፡ ድንጋይ—በእጁ ላይ ይዞ፡ ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ጎትቶ፡ እስኪሞት ድረስ አረደው ቆረጠው። ጸጉሩም በገዛ ደሙ ታጠበ። በገዛ ደሙ ተንከባለለ። ያም ጥላ ነበር።

72 በዚያ ቀን በቀራንዮ የሞተው፡ በገዛ ደሙ የተንከባለለ በጉ ግን፡ የእግዚአብሔር በግ እንጂ፡ የዚህች ምድር በግ፡ አልነበረም። እርሱ በዓለም፡ ታረደ፡ ተቆረጠ፡ ተመታ፡ ተተፋበት፡ በጥፊ ተመታ፡ ተደበደበ፡ ሁሉ ነገር ሆነ፡ ደሙንም በጸጉሩ በኩል ይንጠባጠብ ነበር።

73 የአቤል በግ ሲሞት፡ አቤል የማይሰማው ቋንቋ እየተናገረ ሞተ። እያንቃረረ ነበር።

74 የእግዚአብሔር በግ በዚያ ቀን በቀራንዮ ሲሞትም፡ ማንም በማይረዳው ቋንቋ ተናገረ። “አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውኸኝ? ” የታረደ፡ እና የተቆራረጠ፡ የእግዚአብሔር በግ ነበረ።

75 አቤል የሴቲቱን ዘር ባየ ጊዜ፡ በልቡ ያሰበው በግ እርሱን ነበር። ዳንኤል ያየው በግ እርሱ ነው፡ እጅ ሳይነካው ከተራራው ተቆርጦ የወጣ አለት እርሱ ነው። ለነብዩም፡ በመንኮራኩሩ መካከል የነበረው መንኮራኩር እሱ ነው። አስቀድመው የታዩት ነገሮች ሁሉ በዚያው ቀን፡ በቀራንዮዋ ቀን ተገናኙ። ይህም ታላቅ የምስራችን አመጣ። የሰይጣንን ወገብ ሰበረ።

76 በመጀመሪያ፡ ቀኑ ምን ማለት እንደሆነ መፈለግ አለብን። ሁለተኛ፡ ያ ቀን ለእኛ ያደረገልንን፡ አሁን፡ ለእኛ ያደረገውን ማየት አለብን። ሦስተኛ፡ ደረጃ፡ ለዚያ ቀን ምን ማድረግ እንዳለብን እንመልከት። ምን እናድርግ?

77 በመጀመሪያ፡ ከቀናቶቹ ሁሉ የላቀች ታላቅ ቀን ስለሆነች፡ ልንመለከታት ይገባል። የኃጢአት ዋጋ ተከፈለ። የሰይጣን ኃይል ተሰበረ።

78 አሁን በሞላሹ ምን ማድረግ እንዳለብን ማየት እንፈልጋለን። አሁን፡ በሞላሹ፡ ኢየሱስ በቀራንዮ፡ በዚያ ቀን በቀራንዮ ሲሞት፡ የኃጢአታችን ዋጋ

ብቻ ሳይሆን፡ እኛ፡ እንደ ወደቁ አዳም ልጆች የተዋጁ ሆነን፡ ዋጋ ከፍሎ እርሱን እንድንከተል መንገድ ጠርጎልናል። ተፈጥሮን ሁሉ በሚቆጣጠር በመንፈሱ (የመጀመሪያውን አዳምን) አዳምን መንፈስ እንደመራው፡ ከዚያም እኛ (ሁለተኛው አዳም)፡ ወይም የምድር ሰዎች በክርስቶስ የተዋጀን፡ ከቀራንዮ ቀን ጀምሮ፡ እርሱን መከተል እንችላለን። ስለዚህ፡ በቀራንዮ ሲሞት፡ መንገድ ጠርጓል። እኔና እናንተ እንድንኖር፡ ወደ ምድር የመለሰውን፡ መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስን ሰጠ። ለእኛ ቀራንዮ ማለት፡ እሱን መከተል ማለት ነው።

79 አስቀድመን፡ እሱን እንመልከተው፡ ያደረገልንን እንየው። ከዛ በኋላ እኛስ በምላሹ ለእሱ ምን እናድርግለት? እንተ እና እኔ ምን ማድረግ አለብን?

80 እኛ፡ "አይ፡ እኔ—ደስ ይለኛል። ጥሩ ነገር ነው፡" እንላለን። ነገር ግን መቀበል አለብን። እሱን መቀበል ደግሞ፡ የእርሱን አካል ማለትም ክርስቶስን፡ በልባችን መቀበል ነው።

81 ከዛ፡ ከኃጢአት ነፃ እንሆናለን፡ በላያችን ላይ የሚንጠለጠሉ የኃጢአት ማስሪያዎች፡ በጭራሽ አይኖሩም። እግዚአብሔር፡ ኃጢአትን ሰርተን እንደማናውቅ አድርጎ፡ ፍጹም በሆነው መሥዋዕት ፍጹማን አድርጎናል። ምክንያቱም ኢየሱስ፦ "እንግዲህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ፡" ብሎናልና። ከዚያ በኋላ፡ ሌላ የሚሠራ ነገር የለም፡ በእግዚአብሔር ፊት ፍፁማን ተደርገናል።

82 አሁን ግን፡ ሰፍራችንን የሚያስለቅቀን ነገር አለ። ይህም ንቁ ካልሆንን፡ ወደ ኋላ ለማየት ወደ ነበርንበት እንመለሳለን። ወደ ኋላ ዞረን ወደ ነበርንበት ከተመለከትን፡ መሰዋዕቱ ለእኛ ትርጉም አይኖረውም። ኦ፡ ቤተ ክርስትያን ሆይ፡ አይታያችሁምን? እኔ አልችለውም... ይህን ስራ አልሞክረውም። እኔም፡ እናንተም አንችለውም። መሞከር አያስፈልግም። ወደኋላችሁ ያደረጋችሁትን እስካያችሁ ድረስ፡ ከጅምሩ፡ ወድቃችኋል። ነገር ግን ያደረጋችሁትን አትመልከቱ።

83 ያቺ ቀን በቀራንዮ ያደረገችላችሁ ብቻ ተመልከቱ። ዕዳችሁን ከፍላለችና። ጥያቄው ይመለሳል። "ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ቢቀላ፡ እንደ አመዳይ ትነጻለች፡ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።" ከዚያ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። ፍጹም ኃጢአት አልባ ናችሁ። ያደረጋችሁት ወይም የተደረገው ምንም ቢኖር፡ አሁንምን ኃጢአት አልባ ናችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ እስከተቀበላችሁ ድረስ፡ ኃጢአታችሁ ተሰርዮላችኋል። ማንኛውም ነገር **ይቅር** ተብላችኋል "ተሰርዮላችኋል ተረስቶላችኋል።"

84 ከዛስ ምን ያደርገናል? ከዚህ ሁኔታ በኋላ፡ እንድትከተሉት፡ እርሱ ያደረጋትም እንድታደርጉ፡ መንፈሱን፡ ይሰጣችኋል፡ ሌሎችም ይከተሉታልና። እርሱ አንድ ሰው፡ ፍጹም ሰው ነበር። ነፍሱን ሰጠ፡ ለእናንተም ምሳሌ አደረገ። ታዲያ አሁን ምን ማድረግ አለብን?

85 አሁን፡ ከሁሉ አስቀድሜ፡ መናገር የምፈልገው፡ ኢየሱስ በፍጹም ለራሱ አልኖረም። ህይወቱ ለሌሎች የተኖረ ህይወት ነው። ይህ፡ ፍጹም የሆነ፡ ዘለአለማዊ ህይወት ነው። ወደ ቤተ ክርስትያን ሄጄ፡ መልካም ነገሮችን ስራሁ ስትሉ፡ መልካም ነው። ህይወታችሁ ለራሳችሁ ስትኖሩት ግን፡ የዘለአለም ህይወት የላችሁም። የዘላለም ሕይወት፡ ለሌሎች መኖር ነው። በእግዚአብሔር

በግ በመጣ ጊዜ አረጋግጦታል። እሱ ኖረ፡ የዘለአለም ህይወትም በርሱ ዘንድ ነበረች፡ ለራሱ አልኖረውምና። ለሌሎች ኖረ እንጂ። እናንተም የዘለአለም ህይወት የምትቀበሉት፡ ያቺን ቀን በመቀበል ነው፡ ከእንግዲህም ለራሳችሁ አትኖሩም። ለሌሎች እንጂ።

86 አንድ ሰው እንዲህ አለ፦ “ማንም ሰው በክፉ ስም ሲያነሳችሁ፡ ለምን ትበቀላላችሁ? ” ያን ሰው እንድትዋጁት፡ ለሌሎች ትኖራላችሁ እንጂ። ለራሳችሁ’ኮ አትኖሩም። ልጆች ትሆናላችሁ። የችግሩ ችግር ግን፡ ቤተ ክርስቲያን ልጆች መሆናቸውን ረስታለች። ልጅ ነህ። የክርስቶስ ሰፍራ ተክተሃል። ልጅ ስለሆንክ፡ ለራስህ አትኑር። ለሌሎች ኑር።

87 “ይሁን፡ ወንድም ብራንሃም፡ **ይህ** ወንድም መልካም ሰው ስለሆነ፡ ለሱ መኖር እችላለሁ።” ያ ትክክል አይደለም።

88 ለሚጠላህ ሰው ኑር። ቢችል ለሚገድልህ ለዚያ ሰው ኑር። በእርሱ ላይ ያደረጉት ይህንኑ ነው። እነርሱ ገደሉት፡ እሱ ግን ያድናቸውም ዘንድ ሞተ። የዘላለም ሕይወት ይህ ነው። ይህ ነገር፡ በውስጣችሁ በሆነ ጊዜ፡ ፊታችሁን ወደ ሰማይ ማየት የሚጀምረው፡ ያኔ ነው። እናንተ ግን ነገራችሁን ሠዉ፡ በግ ጠጉርን እንደሚሰጥ፡ እራሳችሁን ስጡ። ወደ ቀራንዮ ተመልከቱ።

89 በሰፍራችሁ እንድትገኙ ይህ ይጠቅማችኋል ብዬ አስባለሁ። ተበርናክሉም፡ ህዝቡም ሁሉ ማድረግ ያለበት ይህ ነው፡ ማንነታችሁን፡ እና ዓላማችሁን ፈልጋችሁ አግኙ። ቤተ ክርስቲያን፡ ሙዚቃ ለመጫወት፡ መዝሙር ለመዘመር ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይኬድም:::: ቤተ ክርስቲያን የእርማት ሰፍራ ነው። “ፍርድ የሚጀምረው በእግዚአብሔር ቤት ነውና።”

90 “ራሳችንን እንደሞትን፡ እና ለክርስቶስ ሕያዋን እንደሆንን መቁጠር አለብን።” ስለዚህ፡ እርሱን ለመከተል ራሳችንን ለእርሱ አገልግሎት መሰዋዕት ማድረግ የምንችልበትን መንገድ ጠረገ። እርሱን ከተከተልን፡ እርሱ የኖረበትን ሕይወት እንኖራለን። ድንቅ ነው።

91 ኢየሱስም፡ ስለዚህ ተናገረ። ጥቂት ጥቅሶችን ልስጣችሁ። ተከታተሉ። እንዳያመልጣችሁ። ኢየሱስ፡ ሰዎችን እንደ በግ እና እንደ ፍየሎች በሚለይ ጊዜ፡ ተናግሯል። ፍየሎችንም፡ “በግራ በኩል ቁሙ።” በጎቹንም “በቀኝ በኩል ቁሙ፡” ይላቸዋል።

92 ፍየሎችንም አላቸው፦ “ከእኔ ራቁ። ምክንያቱ፡ ተርቤ፡ አላበላችሁኝም። ታስሬ፡ አልጠየቃችሁኝም። ታርዤ፡ አላለበሳችሁኝም። ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም። ታምሜ፡ አልጠየቃችሁኝም። ስለዚህ፡ ከእኔ ራቁ።”

93 በበጎቹንም፡ ይላቸዋል፦ “ተርቤ፡ አብልታችሁኛል። ታርዤ፡ አልብሳችሁኛል። ታምሜ፡ አገልግላችሁኛል።”

94 አሁን አስተውሉ። ቤተ ክርስትያን ሆይ፡ እያምልጣችሁ። ለዘለአለም፡ በልባችሁ ጠብቁት። ሳታስቡት የሚደረግ ነው! ሰዎች ግዴታን ለመወጣት ብለው አያደርጉትም። መስጠት ስላለበት፡ አንድን ነገር የሚሰጣችሁ ሰው፡ እናንተን ማብላት ስላለበት የሚያበላችሁ ሰው፡ የራስ ወዳድነት አስተሳሰብ አለው። የራሳችሁ ህይወት፡ የራሳችሁ ድርጊት መሆን አለበት።

95 እነዚያ በጎች፡ እንዲህ ማለታቸው እጅግ ይገርማል፦ “ጌታ ሆይ፡ መቼ ተርበህ? አላበላነህስ... መቼ ተርበህ፡ እኛ አበላነህ? መቼ ታርዘህ።ልብስ አለበስንህስ? መቼ ተጠምተህ፡ አጠጣንህ? መቼ ታምመህ ነበር እና፡ አገለገልንህ?”

96 ከቅጽበታዊ ፍቅር የሚነሳ ነበር፡ በነዚያ ውስጥ ህይወታችሁ ይኖራል። እግዚአብሔር ሆይ፡ ቀራንዮ ያደረገልንን ቅጽበታው ነገር፡ ሰዎች እንዲያዩ አድርግ።

“ጌታ ሆይ፡ መቼ ነው? ያንን ፈጽሞ እናውቅም።”

97 ኢየሱስ ዘወር ብሎ፡ ምን እንዳለ ተመልከቱ፡ “በእነዚህም ላይ ያደረጋችሁት፡ ለእኔም አደረጋችሁት።”

98 ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ሕይወት፡ ሁለተኛ ሀሳብ የሌለው። ሳታስቡት፡ ለዚህ ዓለም ነገር ትሞታላችሁ፡ ለክርስቶስ ግን ህያዋን ናችሁ፡ በጎዳናዎቹ ሁሉ ትጓዛላችሁ፡ እነዚህ ነገሮች ቅጽበታዊ ነገሮች ብቻ ናቸው። “እንግዲህ፡ አሁን፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ጌታ፡ ያንን እንዳደርግ ይፈልገኛል።” ሳትሉ፡ እንዲሁ ታደርጉታላችሁ። አይደለምን። የአካሉ ብልት ናችሁ። መንፈሱ በውስጣችሁ አለ፡ እሱ እንዳደረገ እናንተም እንዲሁ ታደርጋላችሁ። አህ! ተረዱት።

99 “ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፡ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።”

100 “የአባቴን ፈቃድ የሚፈጽሙ ሁሉ እንጂ፡ ‘ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡’ የሚለኝ ሁሉ፡ የሚገባ አይደለም፡” ከልባቸው፡ በነጻነት።

101 አሁን፡ በቀራንዮዋ ቀን ያንን ዋጋ ተከፍሏል፡ ስለዚህ እንዲሁ መሆን እንችላለን።

102 እንዲህ አትበሉ፦ “አየህ፡ መበለቲቷ ጆንሰን በአንድ ወቅት... ከሰል አልቆባት፡ ሄጄ ከሰል ገዛሁላት። ልንገርህ፡ የሱፍ ልብስ የሚያስፈልገው ወንድም አይቼ ልብስ አመጣሁለት። እግዚአብሔር ይባረክ! እኔ ክርስቲያን ነኝ” አትበሉ። ኦህ፡ ማይ! ራስ ወዳድ፣ ምስኪን፣ ድኃ፣ ግራ የገባው። ግብዝ ነህ።

103 “የቀኝ እጅህ ስራ ግራህን፡ የግራህም ቀኝህን እንዲያውቅ አትፍቀድ።” እንዳደርግከው ሳታውቅ ማድረግ እስክትጀምር ድረስ፡ በክርስቶስ ቅጽበታዊ ሞት ትሞታለህ። ተፈጥሮህ ነው። ስሪትህ-ነው። ሳታውቀው፡ ታደርገዋለህ። በቃ በአንተ ውስጥ የሚኖረው ሕይወት ነው። ራስህን ሙሉ በሙሉ ለመንፈሱ ሰጥተሃል፡ በአንተ ውስጥ የሚኖረው እርሱ ራሱ ነው። ኦህ፡ የተባረከው ያመንፈስ ይሰማሃል፡ ያ ህይወት! “የምኖረው እኔ አይደለሁም፡” አለ ጳውሎስ፡ “ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፡” በቃ ቅጽበታዊ ነው።

104 “አየህ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ልንገርህ፡ እኛ ክርስቲያኖች ነን። **እነዚያን** ሰዎች ረዳናቸው። **ሰዎቹን** ረድተናቸዋል።” ኧረ፡ እንደው! ታሳፍራላችሁ። ያ ክርስትና አይደለም።

105 ክርስትና ቅጽበታዊ ነው። መደረግ ያለበት ነው። ወድያውኑ፡ መሉ ለሙሉ ትረሱታላችሁ፡ “እኔ አይደለሁም።” በቃ ሂድና አድርግ።

106 ክርስቶስ ነፍሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ። ሕዝብን እንደሚያገለግል፡ ራሱን፡ ለሕዝብ ሰጠ። ነፍሱን፡ በነጻነት ሰጠ። ከእርሱ ከራሱ ሊያደርግ አልተገባውም። ለመደነቅ አላደረገውም። “አሁንም፡ ወንድሞች ሆይ፡ እኔ ስለ እናንተ ልሞት መጥቻለሁና፡ አብዝታችሁ ስለ’ኔ ማሰብ አለባችሁ፡” አላለም። አንድም ቃል አልተናገረም። እግዚአብሔር በእርሱ ዘንድ ስለ ነበረ፡ እንዲሁ፡ ሞተ።

107 ሌሎችን እንድንመለከት የሚያደርገን፡ በእናንተ ውስጥ ያለው እግዚአብሔር፡ በእኔ ውስጥ ያለው እግዚአብሔር ነው። በአንድ በኩል፡ በጎች።

108 አንዳንዶች “አየህ፡ ጌታ ሆይ፡ **ይህን** አደረግሁ። ጌታ ሆይ፡ **ያንንም፡** አደረግሁ፡” ይላሉ።

109 እርሱም “እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ። እኔ አላውቃችሁም፡” ይላቸዋል።

110 ቤተ ክርስቲያን ወደ እነዚያ መሠረታዊ እውነታዎች፣ ማለት ለማድረግ የሚሞከር፡ ያንን ነገር ለመፈጸም እራስህን የምታዘጋጅበት ነገር አለመሆኑን ወደ ማወቅ ባደገች። በውስጣችሁ የሚወለድ ነገር ነው።

111 ይቅርታ አድርጉልኝ፡ እናንተ የጴንጤቆስጤ ወዳጆቼ። እኔም ጴንጤቆስጤ ነኝ። ነገር ግን የጴንጤቆስጤ ጓደኞቼ አንድ ነገር ላይ ደርሰዋል፡ ይህም—ጩኸትን ለማንሳት፡ ፈጣን ሙዚቃ መጫወት፣ አንዳንድ ባንዶች መምታት፣ ወይም ማጨብጨብ፡ አታሞ መምታት ጀምረዋል። ያ ስሜት ብቻ ነው። ወደ ጦርነት ከመሄዳቸው በፊት ባንዶች ይጫወታሉ። ሰዎችን የጦርነት ስሜት ውስጥ ያስገባሉ። በሙዚቃ አምናለሁ። በማጨብጨብ አምናለሁ። በእነዚህ ነገሮች አምናለሁ። ያ በትክክል እውነት ነው። ያንን ሊኖረን ይገባል።

112 ነገር ግን ትልቁን ነገር ትታችኋል፡ እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ የሚኖረውን ራስን-የመሠዋት ህይወት፡ ነገሩ ትክክል ስለሆነ ብቻ በቅጽበታዊ እንዲሁ አድርጉት። ከዛ በኋላ ማድረጋችሁን አታስቡ፡ ዝም በሉና ሂዱ። በቃ ተዉት። ከዚያ ተመልከቱ፡ ምን እንደሚከሰት ታያላችሁ። አንተ… ብቻ… አውራው ጎዳናውን ይዘኸዋል። ቀራንዮ ለእናንተ ይሄው ነው፡ አውራ ጎዳናው ላይ፣ ያን ቀን ተከፈተላችሁ።

113 እንግዲህ፡ አሁን አስታውሱ፡ ግማሽ ፍየል እና ግማሽ በግ መሆን አይቻልም። መቀላቀል አይችሉምና።

114 አሁን፡ ብዙ ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡- “አዎን፡ ታውቃለህ? በኛ በእድራችን ውስጥ ድርጅት አቋቁመናል። እኛ፡ ድሆችን እንረዳለን። **ያንን** እናደርጋለን ይላሉ።” መልካም ነገር ነው፡ ይሁን እንጂ ስለ ስራህ ጥሩምባ እየነፋህ ነው። እንዲህ አታድርግ።

115 “ምጽዋትህን በድብቅ ስጥ፡” አለ ኢየሱስ። ማለት ጠምቶህ፡ የሚጠጣ ውሃ ለማምጣት፡ እንደምትሄድ አይነት፡ ቅጽበታዊ ነው። በቃ ጠምቶሃልና። አጠገብህ ያለው ሰው ከተጠማ፡ ስለ እርሱም፡ ታስባለህ። አጠገብህ ያለው ሰው ሲያጣ፡ አንተ ራስህ እንዳጣህ አድርገህ ታስብለታለህ። ከዛ ህይወትህን ብቻ ቀጥል። አታስበው።

እንግዲህ፡ ግማሽ ፍየል እና ግማሽ በግ መሆን አይቻላችሁም።

116 ስለዚህ እንዲህ ብትሉ፦ “እየህ፡ ቤተክርትያናችን’ኮ ድርጅት አቋቁማለች። ድሆችን እንረዳለን፡ **ይሄን** እናደርጋለን። **ያንን** አድርገናል፡ **ሌላም** እናደርጋለን።”

117 የክርስቶስን ህይወት ሳይኖራችሁ፡ ይህ ሁሉ ቢኖራችሁ፡ እንደው በከንቱ ታደርጋላችሁ። ኢየሱስ… ጳውሎስ፡ አንደኛ ቆሮንጦስ 13 ላይ እንዲህ አለ፡ “ድሆችን ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፡ ሥጋዬንም መሥዋዕት አድርጌ ባቃጥል፡ ምንም አይጠቅመኝም።”

118 ይህ፡ ከባድ ነገር ነው፡ ግን እውነት ነው። ወደ እውነታው፡ ቀራንዮ ወዳደረገላችሁ እውቀት መምጣት አለባችሁ። አይተነው፡ “ኦህ፡ አዎን፡ ጥሩ ነው፡” እንላለን። እንደዛ አይደለም። የእግዚአብሔር ልጅ ለመሰቀል ወደ ቀራንዮ መሄድ ከነበረበት፣ የሚከተል ልጅ ሁሉ ወደ ቀራንዮ መሄድ አለበት። የራሱ ቀራንዮ ሊኖረው ይገባል። የቀራንዮ ቀን ሊኖራችሁ ይገባል። የቀራንዮ ቀን ሊኖረኝ ይገባል። የኃጢአትን ጥያቄ የሚመልስ ይህ ነው። ከሰባኪው ጋር እጅ በመጨባበጥ፡ ቤተ ክርስቲያን ሰላም መባባል አይመልሰውም፡ በመወለድ የሚገኝ እንጂ፡ በደብዳቤ አይገኝም፡ በሙያተኛነት አይገኝም። መወለድ ስጠን እንጂ። ደብዳቤ ሰጥቶ አያውቅም። ሙያተኛነት ሰጥቶ አያውቅም። እኛም የገባነው በዚሁ ነው። ከዚያም፡ ወዲያውኑ፡ የክርስቲያን ሕይወት እየመራን እንገኛለን።

119 አሁን፡ ሌላ አስተያየት። ግማሽ ፍየል፡ ግማሽ በግ፡ እንደዚህ አይነት ነገር የላቸውም። ፍየል ወይም በግ ናችሁ። ግማሽ ፍየል እና ግማሽ በግ አትሆኑም። ወይም ፍየል ወይም በግ ትሆናላችሁ።

120 አሁን፡ ጥሩ ነገሮችን በማድረጋችሁ፡ በዚህ፡ መግባት እንደምትችሉ ካሰባችሁ፡ የቀራንዮ ቀን መኖሩ አስፈላጊነት አይኖረውም ነበር። ህጉ ግን አቅርቧል። የቀራንዮ ቀን መኖር፡ ግን፡ አንድ ነገር አምጥቷል፡ ይህም የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች እንጂ፡ የቤተ ክርስትያን አባላት ሆነን መቅረት እንደማይገባ ነው። የቀራንዮ ቀን ማለት ይህ ነው። እንደ ኢየሱስ መስራት፡ እና ማድረግ፡ መከተልም እንድትችሉ፡ ትርጉሙ ለእናንተ ይህ ነው።

121 ማለት፡ ወንዝ በአንድ ጊዜ ወደታች እና ወደላይ፡ አይፈስም። ወንዝ ዘወትር ወደ አንድ መንገድ ብቻ ይፈሳል። የእግዚአብሔር መንፈስም በአንድ መንገድ ብቻ ይወርዳል። ሌሎች ነገሮችን ከሱ ጋር አያዋህድም። አወራረዱ አንድ ነው።

122 አሁን እየጨረስን፡ ኢየሱስን ተመልከቱት። ኢየሱስም “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ፡ ከዚህም የሚበልጥ ታደርጋላችሁ፡ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፡” አለ።

123 ይህ እየተናገርኩት ያለሁት እዚህ-ላለች ቤተ ክርስትያን አይደለም። እናንተም ታውቃላችሁ። እነዚህ መልዕክቶች ግን በቴፕ የተቀዱ ናቸው። በዓለም ዙሪያ፡ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ይሰሟቸዋል።

124 ለተቺው አሁን መልሱን እመልስለታለሁ። ብዙ ጊዜ ተብያለሁ… ብዙ ተነግሮብኛል። እነርሱም “ለምን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ታምናለህ? ” ይላሉ፤ ኢየሱስም አለ፦ ‘እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ፡ ከዚህም የሚበልጥ ታደርጋላችሁ፡ እኔ ወደ አባቴ እሄዳለሁና።’”

125 ምን ያህል ክፉ ትሆናለህ፡ ጃል? በሰነ መለኮት ዕውቀትህ፡ ሰለነገሮች ባለህ አይምሮአዊ መረዳት፡ ከመለየት ጸጋ ተለይተህ ምን ያህል ትንከራተታለህ? የጠፋህ ደግ ወዳጄ ሆይ፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈሳዊ ሁኔታ መተረጎሙን መረዳት አትችልምን?

126 ኢየሱስ ከተማሩ፣ አስተዋዮች፣ ከጥበበኞች፣ እና ከአስተዋዮች ሰውሮ፣ ወደ ቀራንዮ ለሚመጡ ሕፃናት ስለገለጠላቸው አብን አመሰገነ።

127 ተከታተሉኝ። ኢየሱስ አለ። እንዴት እንዳስቀመጠው ተከታተሉ። “እኔ የማደርገውን ሥራ፡” አሁን እየሰራቸው ነው። “አሁን የማደርገው ሥራ፣ ድውያንን መፈወስ፣ ሙታንን ማስነሳት፣ የዕውሮችን ዓይን መክፈት፣ እናንተም እነዚህ ሰራዎች ታደርጋላችሁ። በእኔ ብታምኑ እነዚህ ነገሮች ታደርጋላችሁ። ሰራዎቹን ትሰራላችሁ። እኔም ወደ አባቴ እሄዳለሁና፡ ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ።”

128 “ጥቂት ጊዜ አለ፣ አለም ከእንግዲህ አያየኝም፣ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ። ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ በእናንተ ውስጥ እሆናለሁ፡ ያለ አጽናኝ አልተዋችሁም። አብን እለምናለሁ፡ ሌላ አጽናኝ ይልክላችኋል፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ዓለም የማይቀበለው፡ እናንተ ግን፡ ትቀበሉታላችሁ።”

129 አሁን ተተከታተሉ። “የሚበልጥ” ሰራዎች፡ ኃይሉን ቤተ ክርስትያን ውስጥ መኖሩ ነው፡ የታመሙትን በጸሎት መፈወስ፣ በጸሎት አጋንንትን ማስወጣት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለሚያምኑ የዘለአለምን ህይወት ማካፈል። ህይወትን ማካፈል ይቻል ዘንድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በቤተ ክርስቲያን እጅ ተሰጠ። ኦ! ቀራንዮ ማለት ያ ነው። የጎበጡ፣ እና የተዋረዱ ወንዶች እና ሴቶች ወስዶ፡ መንፈስ ቅዱስን ለሚታዘዙ አማኞች በመስጠት፡ ህመምተኞችን እንዲፈውሱ ዘለአለማዊ ህይወት ማካፈል እንዲችሉ፡ እምነት ያለነበራቸውን ሰዎች፡ አማኞች አድርጎ፡ መንፈሳዊ፡ እና ዘለአለማዊ ህይወት አካፍሎ፡ የእግዚአብሄር ወንድ እና ሴቶች ልጆች ይሆኑ ዘንድ አነሳቸው።

130 “ይህች ታምማ እዚህ የተኛች ሴት፡ የእምነት ጸሎት መጸለይ በመቻሌ ትፈወሳለች፡” ማለት፡ እንዴት ድንቅ ነው፡ በጣም ጥሩ ነገር ነው፡ ያኔ ያደርግ የነበረው ይህ ነው፡ “ግን፡” አለ፡ “ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ፡ ኃይል እሰጣችኋለሁ፡ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ማስነሣት ሳይሆን፡ ነገር ግን ዘለአለማዊ የሆነውን፡ የዘላለም ሕይወት ትሰጡት ዘንድ ነው።”

131 ምስኪን፣ ዕውር፣ ድሆች ሆይ፡ እንዴት ሳታችሁ? “የሚበልጠው” ነገር ምን እንደሆነ አይታያችሁምን? ከመቼውም ጊዜ በላይ በልጦ ሊደረግ የሚችለው ነገር፡ የዘላለም ሕይወትን ለሰዎች መስጠት መቻል ነው። የዘላለም ሕይወት ምንድን ነው? እርሱ የኖረው ሕይወት፣ በእርሱ ውስጥ የነበረ ሕይወት፣ ያንን ለሌሎች ማካፈል ነው። ሰው ይህን ማድረግ ይችላል? የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ይችላል።

132 ኢየሱስም አለ፦ “ኃጢአቶቻቸውን የምትተውላቸው፡ ይተውላቸዋል። ኃጢአት የያዛችሁባቸው ሁሉ፡ ይያዝባችኋል።”

133 አሁን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እና ሌሎች የተሳሳቱት ትልቅ ስሕተት ይህ ነው። ወጥተው “ኃጢአትህን ይቅር ብያለሁ” ይላሉ። እንደዚያ አይደለም።

134 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአታቸው የተሰረየላቸው እንዴት ነበር? ጴጥሮስ ለጥያቄው መልስ የሰጠው፡ በበዓለ ሐምሳ ቀን ነው። እነርሱም አሉ፦ “እንድን ዘንድ ምን እናድርግ? ያገኛችሁትን ማግኘት እንችል ዘንድ ምን እናድርግ? ” ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነገራቸው። ማዘዣውን ጻፈላቸው።

135 “እያንዳንዳችሁ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ንስሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተጠመቁ፡” አላቸው። ስለ ምን? ስለ ኃጢአታችሁ ስርየት። “የሚበልጡ” ስራዎች ማለት እነኚህ ናቸው።

136 ዛሬ ጠዋት፡ ሰንቶች ሰባኪዎች፡ ቃሌን በማግኔቲክ ቴፕ እየሰማችሁ ያላችሁ፡ ዛሬ ማለዳ፡ ወደ ቀራንዮ ለመሄድ ሰንቶች ፈቃደኞች ትሆናላችሁ? እግዚአብሄር ያደረገላችሁን ማየት የምትወዱ። የሐይማኖት ተቋም ስርዓቶች ትታችሁ፡ ወንጌልን የምትሰብኩ። ሃሌ ሉያ! አሁን በእቅፋችሁ ላይ ነው። ምን ታደርጉታላችሁ?

137 “ንስሐና የኃጢአት ስርየት፡ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ፡ ለዓለም ሁሉ በስሙ መስበክ አለበትና።” ሃሌ ሉያ! ክብር ይሁን! ይሄው ነው።

138 ቀራንዮ ለእናንተ ምናችሁ ነው? ያ ቀን ምን አደረገላችሁ? በአንዳንድ ስነ መለኮት፡ ይጠቀጥቃችኋልን? የተጠቀጠቀ ሸሚዝ ያደርጋችኋልን? ወይስ ፈጽሞ የተሸጠ፡ ክርስትያን ያደርጋችኋል? ሃሌ ሉያ!

139 የኃጢአት፡ ስርየት! “ከዚህ የሚበልጥ ስራዎች ታደርጋላችሁ።” “ታደርጋላችሁ” የሚለውን፡ ለማን እንደሆነ አይታችኋል ወይ? “ከዚህ የሚበልጡ ሥራዎች፡” በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ኃጢአትን ማስተሰረይ።

140 በስርዓቶች እና በሐይማኖት ተቋማት፡ ወዘተ ግን፡ ወደ ውስንነት ያመጣችኋል፡ አሁንም ዓለምን ታገለግላላችሁ። የሆነ ነገር ስለተናገረ ብቻ፡ ወደ ቀራንዮ የመጣና ትልቅ የሆነ፡ ወንድ ወይም ሴት ካለ ንገሩኝ። በዚያ ቀን በቀራንዮ፡ በቀራንዮ ብርሃን ፊት፡ ይሄን ማየት ከቻላችሁ ንገሩኝ። ቀናችሁን በቀራንዮ አሳልፋችሁ፡ የተጠቀጠቀ ሸሚዝ እንዴት ትሆናላችሁ? እንዴት የድርጅት አሻንጉሊት ሆናችሁ፡ ሰው-ሰራሽ አስተምህሮዎችን ትሰብካላችሁ? ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቃል እንድታዋርዱ ለምን አላስቻላችሁም? ወደዚያ ብትሄዱ ኖሮ፡ ትሁታን ሆናችሁ በተመለሳችሁ ነበር። በድርጅታችሁ ውስጥ፡ በኮፍያው ላይ ላባ የተሰካለት ታላቅ ሰው ለመሆን እንዴት ትፈልጋላችሁ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተቆረሰ-ሥጋ፣ ለተተፋበት ፊት፣ እስከ እፍረትና ውርደት ድረስ ራሱን ባዋረደ ጊዜ? ልብሱንም ገፈው፡ በዓለም ፊት፡ ሰቀሉት። “እርሱ ነውርን ንቋልና።” ወደ ቀራንዮ ሄዳችሁ እርሱ ከነበረው በተቃራኒ ሆናችሁ፡ በነውር፡ በእፍረት፡ እንዴት ትመለሳላችሁ?

“ኧረ፡” “ቢያባርሩኝስ፡” ትላላችሁ። እስቲ ያባርሯችሁ።

141 ቀናችሁን በቀራንዮ አሳልፉት፡ እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር የራሱ መንገድ ያወጣል። ደግሜ ልናገር። ቀናችሁን በቀራንዮ አሳልፉ፡ እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር የራሱ መንገድ ያወጣል።

እንጸልይ ።

142 አቤቱ፡ አምላኬ ሆይ፡ ሁላችንም አሁን ወደ ቀራንዮ ውሰደን። ጌታ ሆይ፡ ከራስ ፍርሃት፡ ሰውን ከመፍራት እገሌ የሚናገረውን ከመፍራት አርቀን። በእርሱ

ላይ፡ አለም ሁሉ ሳቀ፡ ተሳለቁበት። እርሱ ግን እስከ ሞት ድረስ፡ ታዛዥ ነበር። ለመዋረድ፡ ታዛዥ ሆነ። ለማእከላዊ መንግሥትም ቢሆን፡ ታዛዥ ነበር።

143 ሰይጣንም ይህችን ምድር ሲመታ፡ በዚህ ምድር ላይ ገዥና ባለ ሥልጣን እንደሆነ እንገነዘባለን። በጌታችንም ፊት መሰከረ፡ እንዲህም አለ። “እነዚህ መንግስታት የእኔ ናቸው። የምፈልገውን አደርግባቸዋለሁ።” እና ከዚያ ቀን ጀምሮ፡ እስከዚህ ድረስ፡ ይህ ዓለም፡ በእርግማኑ፡ በረገመው ሰው ስር እንደተገዛ እንገነዘባለን።

እኛ ግን፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ ሆይ፣ ያልተረገመች መንግሥትን እናገለግላለን።

144 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ አሁን ባለው ዓለም ሰዐል ውስጥ—የሰራኸው ድንቅ ሰራ፡ እንዴት ድንቅ ነው። እነዚህ ታላላቅ ሥዐሎች፣ እንደ **አሥር ትእዛዛት**፡ እና የመሳሰሉት፡ ወጥተው፡ ወንዶች እና ሴቶች እንዲያዩት፣ ወደ ቤተ ክርስትያን ጉባኤ የማይሄዱትን፡ እንዲያዩ አድርገሃል። የእግዚአብሔር መንገድ፡ በዓለም የተጠላ መንገድ ነው። ምክንያቱም እኛም እንደ... ኮሚኒዝም ወደ ሩስያ እንደተወሰዱ ሆነናልና።

145 በዚህ ዓለም ውስጥ ነን፡ የዚህ ዓለም ግን አይደለንም። ወደ ቀራንዮ ሄደናል። የራሱ ከሆኑት ጋር እንቆጠር ዘንድ፡ ስለ እግዚአብሄር መንግስት፡ እራሳችንን ሰቅለናል። ዓለም ምንም ቢል፡ በጌታ ከተናቁ ጥቂቶች ጋር መንገዱን እንይዛለን። ወደ ትንሣኤ እንቀጥላለን፡ ያም በቅርብ እንደሚሆን እናምናለን፡ ጌታ ሆይ፣ ይህንን አለምን ድል ወደሚነሳ መንግስት የማንወሰደው እስከመቼ ይሆን። ዳንኤል አስቀድሞ፡ አለምን ሁሉ ተሰባብሮ፡ ሁሉ እብቅ ሲሆን፡ እንደ በጋ አውድማ ንፋሱ ሲነፍሰበት አይቷል። ተራራው ግን፡ ድንጋዩ ግን፡ ምድርን የሚሸፍን ትልቅ ተራራ ሆነ። ድንጋዩም ይመጣል። አምላክ ሆይ፡ የዚህ አካል መሆን እንፈልጋለን። ራሳችንን እንካድ፣ መስቀላችንን በየቀኑ እንሸከም፣ ለክርስቶስ እንኑር፣ ለሌሎች እንኑር። ስጠን፡ ጌታ ሆይ።

146 ምናልባት ዛሬ ጠዋት፡ እርሱን እንደ አዳኝ የማያውቁት ጥቂት ሰዎች ቢኖሩ፡ በመዝጊያው ጸሎት እንዲታሰቡ ከፈለጉ፡ ምናልባትም ይህ ቀን የቀራንዮ ቀናንችሁ እንዲሆንላችሁ ብትወዱ፡ እጆችሁን ወደላይ አንስታችሁ፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ለእኔ ጸልይልኝ። እርሱን እንደ አዳኜ ማወቅ ፈልጌአለሁ።” በሉ። እግዚአብሔር ይባርክህ ወጣት ልጅ። ሌላ ሰው? እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ከኋላ ያለኸው ወንድሜ።

147 እንዲህ የሚል፡ አንድ ሰው ይኖር ይሆን? “እሱን ማወቅ እፈልጋለሁ። ይህ ቀን፡ የቀራንዮ ቀን እንዲሆንልኝ እፈልጋለሁ። ታምሜአለሁ ደክሞኛል። የተወለድኩበት ነገር ይዤ እዚህ አካባቢ ብዞር ምን ይጠቅመኛል? መወለዴ፡ እኔ የተወለድኩት የእግዚአብሔር ልጅ ልሆን ነው፣ እኔ ግን የአለምን ነገር አጥብቄ ይዣለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ልሰቀል። ዛሬ፡ ከክርስቶስ ጋር እንድኖር፡ እና ለሌሎች እንድኖር፡ ራሴን እና ሀሳቤን እንድሰቅል ፍቀድልኝ። ምንም ቢያደርጉብኝ፣ ወይም ቢዘባበቱብኝ፣ ቢያሳድዱኝም፣ ክፉውንም ሁሉ ቢናገሩብኝ፣ ወዘተ፣ ልክ እንደ እርሱ እንደ በግ በትህትና እና በየዋህነት ልሂድ። አንድ ቀንም፣ በመጨረሻው ቀን፣ እንደገና ሊያስነሳኝ ቃል ገብቷል። ያን ቀንም እናፍቃለሁ።” የሚነሱ ሌሎች እጆች ይኖሩ ይሆን? እግዚአብሔር ይባርክህ

ከኋላ ያለኸው፡ አንተንም። እሺ። ሌሎችም ካሉ… እግዚአብሔር ይባካችሁ። እግዚአብሔር ይባካችሁ። ከመጸለያችን በፊት፡ ሌሎች ካላችሁ።

148 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን በሰበከ ጊዜ፡ እንዲህ ተብሏል፦ “ያመኑት ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን ተጨመሩ።” በፍጹም ልባቸው በእውነት አመኑ። አሁንም እጃቸውን ያነሱ ሰዎች፣ በሙሉ ልባቸው አምነዋል ብዬ አምናለሁ። ካመኑም፡ የሚጠብቃቸው የውኃ ገንዳ ተዘጋጅቶአል። የኃጢአቶችን ይቅርታ እንዲደረግ ይፈልጋሉ። እንድንበት ዘንድ ከሰማይ በታች ለሰዎች የተሰጠ፡ ብቸኛው ሰም ይዞ፡ በዚያ ሰም ሊያጠምቃቸው የተዘጋጀ አንድ ሰው አለ።

149 ከጥቂት ጊዜያት በፊት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደጠቀስኩት፣ “ንሰሐና የኃጢአት ሰርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለዓለሙ ሁሉ በሰሙ ይሰበካል” ብያለሁ። በኢየሩሳሌምም፡ ንሰሐና የኃጢአት ሰርየት በተሰበከ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱሳት መጻሕፍትን ተናገሩ፡ እነርሱም፡ “አሰቀድማችሁ፡ ንሰሐ መግባት፣ ከዚያም በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም መጥመቅ፡” ግዴታ ነው አሏቸው። እነርሱ ንሰሓ እንዲገቡ፡ እርሱም ስለሐጥያታቸው ሰርየት እንዲያጠምቃቸው። ያ የሰባኪው ሰራ ነበር። “ኃጢአታቸውን፡ ይቅር ያላችሁላቸው ይተውላቸዋል፡ ኃጢአት የያዛችሁባቸው፡ ይያዝባቸዋል።”

150 አባት ሆይ፣ ዓለም እንዴት እንደነሱ በቁጣ ተነሳ? ለምን ቀላል የሆነውን ወንጌል ማመን አልቻሉም? እንዲያውም፡ በሌላ፡ የውሸት ሰሞችን፣ የውሸት ጥምቀትን፣ የውሸት መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን፣ ከአገልጋዮች ጋር መጨባበጥ፣ የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ የማዕረግ ሰሞችን፡ በመጠቀም፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ በክርስቲያን ትምህርት ውስጥ፡ ፈጽሞ በሌለ በሮማውያን ሰዎች በተሠራ ሰነድ ለመተካት ያመጣሉ። የኃጢአት ሰርየት በኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ፡ በማዕረግ ሰም የለም።

151 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ተመራጭ አለመሆኑን እናውቃለን። መንገድህ ሁሌም እንዲሁ ነበርና። ነገር ግን ወንዶችና ሴቶች፡ ዛሬ ጠዋት፡ ወደዚያ ቀን፡ ወደ ቀራንዮ ቀን ይምጡ። ኢየሱስ፡ ተንቆ፡ በዓለም፡ እና በቤተ ክርሰትያኒቱ፡ ሊወዱት በተገባቸው ሰዎች፡ ወደተዋረደባት፣ ወደተተለተለባት፡ ወደተተፋባት፡ የተሰደበባት፡ የተገፈፈባት፡ ያቺ ቀን ይምጡ። እርሱ ግን፡ በዚህ ሁሉ፡ አፉን አልከፈተም፡ ሄዶም ለዘበቱበት ሰዎች ሞተ።

152 እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ወደ ቀራንዮ ውሰደን። እኛን እብዶች ናቸው ቢሉን፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን አሳስተዋል ቢሉን፡ ሊናገሩን የፈለጉትን ሁሉ ቢናገሩብን፡ እግዚአብሔር ሆይ፣ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ግን ስህተት ነው ማለት አይችሉም።

ኃጢአታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ መሸፈን አይችሉም። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ኃጢአታቸውን፡ እና አለማመናቸው፡ እንደ ሌሎቹ ሰዎች፡ ተወዳጅነት መፈለጋቸውን ይገልጣል። ዛሬ ጠዋት ወደ ቀራንዮ ይምጡ።

153 “ከኢየሩሳሌምም ጀምሮ፡ በሰሙም ንሰሐና የኃጢአት ሰርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ፡ ለአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል።”

የተሰቀለውን ምሳሌ በመከተል፡ ይተፋባቸው፡ ይዘበትባቸው፡ በሃይማኖታዊ ክህደቶች ውስጥ ሊባሉ የሚችሉትን ሁሉ ተብለው፡ የአብያተክትያናት-ሰባባሪዎች፡ መባል ያለባቸውን ሁሉ ይባሉ።

ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ የጌታ ከሆኑት ከተናቁ ጥቂቶች ጋር መጓዝ ይሁንልን። ወደ ቀኝም ወደግራም ሳንዞር፡ እንደ ሐዋርያት እንመላለስ፡ ከልባችንም በጎነት እግዚአብሔርን ማምለክ ይሁንልን። አባት ሆይ፡ ስጠን።

154 አሁን፡ ወደ ጸሎቱ መስመር የሚመጡትን የታመሙትን እና የተጎዱትን ፈውስ። እጆቻቸውን፡ ከልባቸው ጋር፡ የሚያነሱትን ሁሉ፡ አሁኑኑ ንሰሐ ይግቡ። እጅግ ብዙ ጊዜ የፈጁትም፡ በፍጥነት ወደ ውኃው ይቸኩሉ ኃጢአቶቻቸውም ይሰረይላቸው በመሥዋዕቱ ስም፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ኣሜን።

አዳኜ በሞተበት በመስቀሉ ስር፣
ከኃጢአት ለመንጻት ባለቀስኩበት ስፍራ፡
በዚያ በልቤ ላይ የደሙ መረጨት ሆኗል፡
ክብር ለእርሱ ይሁን...

ክብር ለስሙ ይሁን!
ኦ፡ ክብር ለስሙ ይሁን!
ኦ፡ በዚያ በልቤ ላይ የደሙ መረጨት ሆኗል፡
ክብር ለስሙ ይሁን!

በሚያስደንቅ ሁኔታ ከኃጢአት ዳንኩ፣ (እንዴት? )
ኢየሱስ በፍቅር በዉስጤ ኖሯል፡
በዚያ በመስቀሉ ስር... (የእርሱ ከሆኑት እንደ አንዱ)...
በ፡
ኦ፡ ክብር ለስሙ ይሁን!

ክብር ለስሙ ይሁን!
ክብር ለስሙ ይሁን! (ድንቅ ስም!)
ኦ፡ በዚያ... በልቤ ላይ የደሙ መረጨት ሆኗል፡
ክብር ለእርሱ ይሁን...

155 ያ ብቻ የሆነ ነገር አያደርጋችሁምን? በቃ ይለይላችኋል። ተሰፋ፡ ሕይወት፡ የዘላለም ሕይወት ይጭርባችኋል።

156 "ከክርስቶስ ጋር መሰቀል" ምንድነው? ለሌሎች መኖር ነው። ምን ዓይነት ሌሎች? የሚጠሉአችሁ፣ የማይወዷችሁ፣ የሚሳለቁባችሁ፡ ለነሱ ኑሩላቸው፡ አብሯቸው ሁኑ፡ ውደዷቸው፡ "ስለ ስሜ፡ በከንቱ ለሚጠቀሙባችሁ፡ ክፉውን ሁሉ በውሸት ስለሚናገሩባችሁ ጸልዩ። ከእናንተ በፊት የነበሩት ነቢያትንም አሳደዋልና።"

157 የዛሬው ጠዋት መልእክት ምናልባት ቤተክርስቲያንን ይጠቅማል ብዬ አሰባለሁ፡ ቀራንዮ እና ስቅለት እንደሚያስፈልገን ታዩ ዘንድ ያስፈልጋል።

158 አሁን ሁሉም ምን ይደረግ? ሁሉም ተከፍሏል። በዊልቸር ላይ ያለሽ እህት፡ ለታመማችሁ እና ለተቸገራችሁ ሰዎች ሁሉ፡ ሁሉም ተከፍሏል፡ ማድረግ

ያለባችሁ ብቸኛው ነገር የእናንተ መሆኑን ማመን ብቻ ነው፡ በዚሁ መንገድ ተቀበሉት፡ ትፈወሳላችሁ።

159 አስታውሱ፡ ምን እንደሆነ? ወደ ዓለም ሂዱ፡ ወንጌልን ሰበኩ፡ ህመምተኞችን ፈውሱ፡ የዘለአለም ህይወትን አካፍሉ።

ምን ያህል ታላቅ ይሆን ይሆን፡ የዚህን፡ ሰውዬ ከ—ዕጢ፣ ከካንሰር፣ ከምንም ጋር ይሁን እዚህ ተኝቷል። (ብዙ ጊዜ በረከቱን ሲሰጥ እና ወንዶችን ሴቶችን ሲፈውስ አይተነዋል፡ በዓለም ዙሪያ ሁሉ በአስር ሺዎች እና በሺዎች የሚቆጠሩ የማይወድቁ አጋጣሚዎች፡ ከአልጋዎች፡ ከስትሬቸሮች ሲነሱ፡ አይተናል፡ በካንሰር ጥላቸው ብቻ የቀሩ ሰዎች፡ ዛሬ፡ ተፈውሰው፡ ጤነኞች ሆነዋል።) "እኔ የማደርገውን እነዚህን ሥራዎች እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ"፤ "ከዚህ በላይ፡" ትክክል ነው።

ምን? እኔ ህይወታቸውን ለተወሰኑ ቀናት እንዲያራዝሙ፣ በኢየሱስ ስም እድሜን ሰጥቻቸዋለሁ።

እናንተ ግን፡ "ከዚህ የበለጠ ታደርጋላችሁ፤ በሰሜ የዘላለም ህይወት ትሰጧቸዋላችሁ።" ዋው!

160 በዚህ ውድ ስም ለምን ታፍራለህ? ሰዎች ለምን ይርቃሉ ፊታቸውን ለምን ያዞራሉ? ሰይጣን ነው። በትክክል።

161 "ንስሐና የኃጢአት ሰርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ፡ ለዓለም ሁሉ በሰሙ መሰበክ አለበት።" መልእክቱ መጀመሪያ የወጣበት ቦታ ይህ ነው። ልክ ነው? "ንስሐና የኃጢአት ሰርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ፡ ለዓለም ሁሉ በሰሙ መሰበክ አለበት።"

162 አሁን፣ በመጀመሪያ፣ እሱ እንዳደረገው እናደርጋለን፡ የታመሙትን ለመፈወስ እንጸልይ።

163 በመቀጠል፡ ታላቁ ስጦታ ይኖረናል፡ መጠመቅ ለሚፈልጉ ሁሉ፡ ውኃው፡ ከበስተጀርባ ተዘጋጅቶላቸዋል (የሴቶች ልብስ፡ የወንዶች ልብስ በዚህ ውስጥ አለ)፡ ኃጢአታችሁን ይሰረይ ዘንድ ተዘጋጅታችሁ ቁሙ፡ ምክንያቱም ኃጢአት ሊሰረይ የሚችለው፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሰረት ብቻ እንደሆነ አስታውሱ። "ትድኑበት ዘንድ የሚገባችሁ፡ ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።"

164 ጳውሎስ የተጠመቁትን ሰዎች አገኛቸው። እነሱም ድል አድርገው፡ እየጮሁ ነበር። እርሱም አላቸው፡ "በማን ተጠመቃችሁ? "

እነርሱም "በዮሓንስ፡" አሉት።

እርሱም "ዮሐንሰስ ለንስሓ አጠመቀ፡" አላቸው። አሁን፡ ይህን ተረዱ፡ ለንስሓ ነው፡ ለሐጢአት ሰርየት አልነበረም። ሰንቶች ይሄን ተረድታችኋል? ሁሉም ለንሰሃ፡ ተጠምቀው ነበር እንጂ። ለኃጢአት ሰርየት አልነበረም። ንስሐ ገብተው ነበር፤ "የሰ፡ ሰር፡ እሱ እንደሚመጣ በማመን። እኔም፡ ንሰሃ ገብቻለሁ።" **የንሰሃን ጥምቀት** ተጠመቁ፡ ይህም ማለት "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን" ነው።

165 (መሰዋዕቱ መምጣቱ) **በስሙ** ጊዜ፡ እንደገና በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ ተጠመቁ። እናም ከዚያም፡ እጆቹን በጫነባቸው ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስን፡ ተካፈሉ፡ በልሳኖችም ተናገሩ ትንቢትም ተናገሩ።

166 ያንን ቅዱስ ቃል፡ እንዴት ልትቀይሩት ትችላላችሁ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአዲስ ኪዳን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር ኃጢአቱ ይቅር የተባለበት፡ ወይም በሌላ መንገድ የተጠመቀ አንድ ካለ ቦታው ላይ ጣታችሁን ጠቁሙ።

167 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ አሳዩኝ። ወይም የመጨረሻውን ሐዋርያ ከሞተ በኋላ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ተቋም እስከሆነችበት ጊዜ ድረስ፡ እስከ ሶስት-መቶ-ዓመታት ገደማ በኋላ፡ በአብ፣ በወልድ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ሰም መጠመቃቸውን የሚያሳይ ታሪክ፣ የቤተክርስቲያን ታሪክን ወደ ጠረጴዛዬ አምጡልኝ።

168 አሁን፡ በጥናቴ ውስጥ፡ **የቅድመ-ኒቂያ አባቶች**፡ እና የ... ተመራማሪዎች እና የሁሉም ታሪክ፡ እጅግ ጥንታዊ፡ በዓለም ውስጥ በጣም የተቀደሰ ታሪክ፡ ብቸኛው የማይዛባ ማስረጃ ይዣለሁ።

169 **አወር ሰንደይ ቪዚተርን** ወይም ካተኪዝም ኦፍ ዘ ካቶሊክ ቸርችን አንብቡ፡ የሚሉትን፡ ሰሙት፦ "ምናልባት አንዳንዶች ፕሮቴስታንቶች፡ ወደ ካቶሊክ አስተምህሮ ስለሚስግዱ ይድናሉ፡ መጽሐፍ ቅዱሳቸው፡ 'በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠመቁ' ቢልም፡ እኛ ግን 'የኢየሱስን ሰም' ሉአላዊነት ወስደን፡ 'አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ ቅዱስ' ብለን፡ አስቀምጠነዋል፡ እነርሱም ተቀብለውታል።"

እንግዲህ፡ ይሄን የሚጻረር መጽሐፍ አሳዩኝ።

170 ነገሩ ይህ ነው። ሆኖም ግን፡ ዓለም ሁሉ ይሰግድለታል። ለምን? ወደ ቀራንዮ ደርሰው አያውቁም። ይኸው ነው። አይተውት አያውቁም።

171 ይሳለቁባችኋል ይናገሩባችኋል... ኧረ እንደው፡ "ሆሊ-ሮለር፡" "ኦንሊ ጂሰስ፡" እና የመሰላቸውን አክራሪ ሰሞች ይጠሯችኋል። ምንስ ቢሉ ምን ልዩነት ይፈጥራል? ምንም ቢሉት... ስለጠሩት ነገር ተጨነቀን? እርሱ ተሰቀለ። ለእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር ብቻ ኖረ። በእርሱ ውስጥ የነበረው፡ ያ መንፈስ፡ በእናንተ ውስጥ ቢኖር፡ ሰሙን ተሸክማችሁ፡ ያንኑ ስራውን እንድትሰሩ ያደርጋችኋል። "የምታደርጉትን ሁሉ" (ይላል መጽሐፍ ቅዱስ) "እግዚአብሄርን እያመሰገናችሁ፡ በቃልም ሆነ በስራ የምታደርጉት ሁሉ፡ በኢየሱስ ሰም አድርጉት።"

172 ያንን ሶሥታዊ የአረማውያን ትምህርት፡ ከየት አመጣችሁት? ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን፡ ከካቴኪዝም የወጣ ነው። "ሥላሴ" የሚል ቃል ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አልተጠቀሰም። እንደዚህ ያለ ነገር የለም። የሥላሴ አምላክ የሚባል ነገር የለም። እርሱ አምላክ፣ ብቻውን አምላክ፣ አንድ አምላክ ነው። ድሮም አንድ አምላክ ነው። በሦስት መገለጫዎች ተጠቅሟል፡ አንድ ጊዜ በሙሴ ዘመን፡ እንደ አባት አገለገለ። አንድ ጊዜ ኢየሱስ ሆኖ፡ እንደ ልጅ፡ በሥጋ አገለገለ። አሁን እንደ መንፈስ ቅዱስ ያገለግላል።

ግን አንድ አምላክ ነው። አንዱ አምላክ፡ ሦስት ስም ያለው አይደለም። ሦስት መዓርጎች፣ ሦስት መገለጫዎች በአንድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጂ።

173 ከዚህ የተለየ ነገር አረማዊ ነው፡ አይደለም የሚል ካለ ግን እንዲያሳየን እጠይቃለሁ። ትክክል ነው። ለብዙ ዓመታት ከዓመት ዓመት ደጋግሜ ተናግሬአለሁ፡ ሆኖም፡ (እያችሁ? ) እስከ አሁን ድረስ እኔ አለሁ ያለ አንድም ሰው የለም። ለእኔ ያለኝ... በመጀመርያ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ከዛ ቀጥሎ ይሄን በትክክል የሚያረጋግጡ ጥንታዊ ታሪኮች ናቸው። ዲያብሎስ እንዲሁ የሚያደርጋቸው... ? እኔ... እንግዲህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ እንደሚሆኑ መሰክሮባቸዋል፡ "ወደ፡ኔ ካልሳብኳቸው በቀር እንዴት ይመጣሉ?" እኔ የማውቀው ያ ብቻ ነው። ኢየሱስ የተናገረው ነው፡ ስለዚህ...

174 እንዲህ ይሆናል እያልኩ አይደለሁም... ይህን ካልኩ እና እንደዚህ አይነት ስብከት ከሰበክኩ፣ በመካከላችሁ ዝቅተኛው ግብዝ ሰው እሆናለሁ። ትክክል ነው። እውነት እና ህይወት ስለሆነ ይሄን ተናግሬአለሁ። ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን የተጠመቁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሰዋል። በስሙ፡ ሕይወት አላቸው።

175 በስሙ እንጸልያለን፣ በስሙ እንፈልገዋለን፣ በስሙ እንሰብካለን፣ በስሙ እናጠምቃለን፣ በስሙ እንኖራለን፡ በስሙ እንሞታለን፣ በስሙ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንሄዳለን፣ በስሙ እንነሳለን። "በገነት ያሉት ቤተሰቦች በሙሉ ኢየሱስ ተሰይመዋል።" መጽሐፍ ቅዱስም ይላል፤ "በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ ኢየሱስ ተሰይሟል።" እሱ ሲናገር "በአባቴ... ስም መጥቻለሁ" ብሏልና፡

እንግዲህ "እናንተም፡ ስሙ አባት ነው፡" ብላችኋል።

**አባት** ስም አይደለም መዓርግ እንጂ። እሱም "እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡ እናንተ ግን አልተቀበላችሁኝም፡" አላቸው። አሁንስ በምን ስም ነው የመጣው? ኧረ-እህ። በትክክል፡ "... አልተቀበላችሁኝም።"

176 ስለዚህ ይኸው ነው፡ በቃ፡ አዎን፡ ከጥበበኞች እና ከአስተዋዮች ዓይን የተሰወረ ነው። በትክክል፡ ያ ነው፡ ኧህ-ሃህ።

177 ራዕይ ላይ፡ በቀደምለት እንዳስተማርነው፡ የመጀመሪያዋ ድርጅት የሆነችው አሮጌቷ ጋለሞታ ቤተ ክርስቲያን አለች፡ እንዲሁም ከእርሷ የተወለዱ ብዙ ሴቶች ልጆች ነበሯት። እነርሱም ተመሳሳይ ልማድ ያላቸው፡ ተመሳሳይ ነገር የሚያደርጉ ናቸው። የአብያተ ክርስትያናት ህብረት... ከዓለም፡ ከሮማ ቤተ ክርስትያን ጋር እንደተጣመረች ሁሉ—ያኔም፡ በተመሳሳይ መልኩ፡ በተመሳሳይ መርከብ ውስጥ፡ ከባቢሎን ጋር፡ ተጣምራ ነበር።

178 የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ግን (ሃሌ ሉያ!)፣ የተለየች፡ የተጠራች-ቤተ ክርስቲያን ነች። ቤተ ክርስቲያን እንዴት ተገነባች? ይህንን እንዴት ታውቃላችሁ? ይህ እውነት መሆኑን እንዴት ማወቅ ይቻላችኋል? እግዚአብሔር ሲገልጥላችሁ ነው። አቤል—በግ እንጂ አፕል አለመሆኑን እንዴት አወቀ? ስለ ተገለጠለት፦ "አቤልም በእምነት የሚበልጥን መሥዋዕት አቀረበ።"

179 ኢየሱስ ከደብረ ዘይት ተራራ በወረደ ጊዜ፦ "ሰዎች እኔ ማን እንደሆንኩ ይላሉ፡" ብሎ ጠየቀ?

አንዳንዶች፦ "ኤልያስ፣" "ሙሴ፣" ወዘተ ይላሉ።

“እኔ ግን እጠይቃችኋለሁ፡ ‘እኔ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ፡’” ብሎ ጠየቃቸው?

ጴጥሮስም “አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ፡” አለው።

180 “በጭራሽ ከሌላ አልተማርከውም... ” አለው፤ በሌላ አባባል (ይህን የምለው፡ ትልቅ ለመሆን ሳይሆን፡ ነጥብ ለማንሳት ነው) “ይህን ከትምህርት ቤቶች፡ ወይም ከሰዎች በፍጹም አልተማርከውም፡ በሰማያት ያለው፡ አባቴ ግን፡ ይህን ገልጦልሃል፤ ይህም እኔ (ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ፡ አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ ቅዱስ አለመሆኔ ነው)። በዚህ ዓለት ላይም (በየትኛው ዓለት? አቤል በሄደበት፡ ያው ዓለት ላይ።)፡ በዚህ ዓለት ላይ፡ በተገለጠው የእግዚአብሔር መንፈሳዊ እውነት ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ፡ የገሃነም ደጆች በጭራሽ ሊያሸንፏት አይችሉም።” ትክክል ነው። ይሞክራሉ እንጂ፡ በፍጹም አያሸንፉም። አያችሁ?

181 ስለዚህ ወደ ቀራንዮ ሂዱና፣ ተሰቀሉ፣ ተመልሳችሁ ኑና፣ ለጌታ ከተናቁ ጥቂቶች ጋር ለመሆን ምረጡ፡ ከዛ በኋላ ቀጥሉ።

182 አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ሁሉንም ነገር ለአንተ እናስገዛለን። በዚህ ህዝብ ውስጥ፡ ምን እንዳለ፡ እኔ አላውቅም። ጌታ ሆይ፡ አንተ ካልገለጥከው በቀር፡ የማውቅበት መንገድ የለኝም። አሁንም፡ እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ይህን እንድታደርግ አልጠይቅህም። ብቻ በሰዎቹ እቅፍ ውስጥ አስቀምጬዋለሁ። ይኸው በፊትህ ናቸው። ዛሬ ጠዋት ይህ እውነተኛ ቀራኒዮ ይሁን፡ ለራስ-ፈቃድ፡ እና ለራስ-ምኞቶች እና ለትልቅ የኑሮ ነገሮች፡ እውነተኛ መስቀል ይሁን።

183 ወንዶች ትሑታን ይሁኑ፡ ለጌታ ከተናቁት ጥቂቶች ጋር መንገዱን ለመያዝ ፈቃደኛ ይሁኑ። በትህትና ይራመዱ። መንፈሳዊ ወደሚሆን አካል፡ በምድር ወዳለው የክርስቶስ ሰማያዊ አካል፡ ወደ ታላቁ የእግዚአብሔር መንግስት፡ ወደዚህ ወደ መንግስቱ የተወለዱ ይሁኑ፤ “በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።”

184 ባርከን፡ ጌታ ሆይ። ጥቁር ቢሆን፣ ነጭ፣ ቢጫ፣ ቡናማ፣ ወንድ ወይም ሴት፣ ባርያ ወይም ነጻ ይሁን፡ ሁላችንም አንድ-መንፈስ እንድንጠጣ ተደርገናል።

185 ባርከን፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማለዳ፡ እንደው ለሁሉም... በብዙዎቹ መካከል፡ መረዳት ይኖር ዘንድ፡ ማስተዋላቸውን ክፈትላቸው። ከዚያ፡ እንደ አዲስ ቀን ይሆንላቸዋል፡ ፀሀይም ትበራላቸዋለች፡ ሰው ሰራሽ የሰነ-መለኮት የብዥታ ብርሃን ይርቃል፣ የእግዚአብሔር ብርሃንም በመንገዳቸው ላይ ይበራል፣ ውብ የሆነው ብርሃን የሸፈነውን መሸፈኛ ይሰብራል። ክርስቶስ እንዳደረገውም፡ ለሌሎች በመኖር፡ በቅድስናው እውራ ጎዳና መጓዝ ይችላሉ።

186 አሁንም የጸሎቱን መስመር በምጠራበት ጊዜ፡ ዛሬ ጠዋት አገልጋዮችህ፡ ሁላችንም፡ አንዳችን ለሌላው፡ ስንጸልይ፡ እንድትቀባቸው እጸልያለሁ። እናም ዛሬ፡ በዚህ የጸሎት መስመር የሚመጣ ህመምተኛ ሁሉ እንዲፈወስ፡ አድርግ። እንደ ዓይነ-ሸውራራዋ ሴት ልጅ፡ እንደ ትንሹ ወንድ ልጅ፣ እና... እንደዚያች አሮጊት ሴት፣ እና—እንደ ወንድም ራይት፡ እና ብዙዎቹ በጌታ፡ ዘንድ፡ በብዙ መከራና ዶክተሮች ሊፈውሱት በማይችሉት በሽታ ተይዘው፡ (ከሳምንት በፊት) እንደመጡ፡ እና ዛሬ ግን፡ እነሆ ዛሬ፡ ደህና እንደሆኑ ይሁንላቸው።

187 እግዚአብሔር ሆይ፡ ወንዶችም ሴቶችም ስለገዛ ሐሳቦቻቸው እና ስለ አመለካከቶቻቸው በቀራንዮ ለመሰቀል እንደሚሄዱ "የቀድሞ ፈውስ" መሆናቸውን አውቀው በዚያው እምነት ይለፉ። ኢየሱስን ከመቃብር ያስነሳው ሃይል ህይወት ይስጣቸው፡ ትልቅ የእምነት ህይወት ይስጣቸው።

188 ከዛ በኋላም፡ ወዲያው፡ ብዙዎች ለጥምቀት ወደ ገንዳው ይምጡ። በኢየሱስ ስም፡ እንጠይቃለን። ኣሜን።

189 አሁን፡ የጸሎቱን መስመር እና የጥምቀት አገልግሎትን ለማስኬድ ሃያ ደቂቃ ብቻ ቀርቶናል። አሁን የጸሎት ካርዶች የለንም። ከዚያም አግኝተናልና፡ በምንጀምርበት ጊዜ ሁሉ በትልልቅ ስብሰባዎቹ ውስጥ ለመስራት እንሞክራለን። ሁሉንም ነግሬአችኋለሁ፡ አስቀምጠነዋል፡ በቴፕ ይዘነዋል፡ እና በሄድኩበት ቦታ ሁሉ፡ ካሴቶቹ ወደ ፊት ይላካሉ።

190 ምልክቱ ወደ በረከቱን ብቻ የሚያሳይ ነው። ሃሳቡ የነበረው፦ "ለታመሙ ሰዎች ስትጸልይላቸው፡ ህዝቡ እንዲያምኑህ አድርጋቸው ነው።"

እኔም "አያምኑኝም፡" አልኩት።

እርሱም "እነዚህን ምልክቶች እሰጥሃለሁ፡ በዚህም ያምኑሃል፡" አለኝ። እነዚህ ምልክቶቹ በአለም ዙሪያ ሁሉ ለአስር አመታት ደጋግመው ተንቀሳቅሰዋል፡ አንድም ጊዜ አልወደቁም። በእነዚያም፡ በፍጹም፡ ውድቀት የለም። እውነት መሆኑን ስንቶች ታውቃላችሁ?

191 እንግዲህ፡ በምልክቱ ማመን ከቻላችሁ፡ መልእክቱንም እመኑ። ትክክል ነው። የሚያሳየው እሱን ነውና። እግዚአብሔርም መልእክትን በእኔ ውስጥ ያስቀምጥ ነበር (እንዲሁ ፍጹም ይሁን፣ ግን ምን… ) ውሸትን እነግራችኋለሁን? እግዚአብሔርም እንዲህ እንዳደርግ አይፈቅድልኝም። ኖ፡ ኖ። ኖ፡ ሰር። እውነት እላችኋለሁ።

192 አሁን፡ በዚህ ረድፍ ላይ ያላችሁ፡ እንዲጸለይላችሁ፡ የምትፈልጉ ሁላችሁ፡ በዚህ በኩል ሁኑ፡ ከፈለጋችሁ፡ እዚያ ጋር፡ በቀኝ በኩል ተሰለፉ። እኛ በምንጸልይበት ጊዜም ህዝቡ እንዲያልፍ ያስችለዋል። ከዚያም ወጣቶች—ወንዶች፡ አስተናጋጆች ጠርተን እንዲከታተሉ እንደርጋለን፡ በዚህ በኩል አድርገው፡ ወደዚህ አቅጣጫ ሲመጡ፡ ከኋላ አካባቢ አምጥተናቸው፡ በዚያ በኩል እንዲመጡ እንደርጋቸዋለን። ሁሉም ይጸልይለታል።

193 [አንድ ሰው ወንድም ብራንሃምን አነጋገረ።—አርታዒ።] ኦህ፡ ኖ፡ ናው፡ አላደረግኩም። ደህና፡ በፈለከው ጊዜ። ችግር የለውም። አንተም ልታመጣት ትችላለህ፡ አንተም… እኔም… አሁን ወይም በኋላ፡ እሷ በፈለገች ጊዜ፡ ልናመጣት እንችላለን፡ ችግር የለውም።

194 አሁን፡ ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች የምንችለውን ያህል፡ ጸጥ እንበል። ሁላችሁም፡ መጽሐፍ ቅዱስ—ምን ብሏል፡ አሁኑኑ እንድታስቡ እፈልጋለሁ? "የእምነት ጸሎት ድውያንን ትፈውሳለች።" ትክክል እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ፦ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተም ታደርጋላችሁ" እንደሚል ስንቶች ታውቃላችሁ? ስራዎቹስ ምን ነበሩ? "ይህን ማድረግ እንደምችል ካመንክ እችላለሁ፡" ብሏል። ልክ ነው?

የእኔስ ጥያቄ ምን ነበር? "እያምኑኝም የሚል ነበር።"

እርሱ ግን፦ 'እነዚህ ምልክቶች እንዲያምኑ ያደርጓቸዋል አለኝ።"

195 አሁን፡ ካመናችሁ፡ የነጻ መውጣት ሰዓታችሁ ነውና፡ ተዘጋጁ። ልክ ከሀጢያት እንደሚሆን ሁሉ፣ የአንድ አምላክ ቃል ኪዳን ያው ነው።

196 አሁን፡ ከኒው አልባኒ የመጣች፡ የሆድ ህመም የታመመች፡ ምስኪን ሴት፡ እዚህ በፊቴ አለች። ወደ ወንበሯ—እንድትመለስ፡ መጀመርያ፡ ለእሷ እንጸልያለን። አሁን፡ ሁላችሁም፡ አሁን፡ በፍጥነት። እዚህ ወንድሞች እንዲረዱኝ፡ እፈልጋለሁ። እና አሁን ለጸሎት፡ ለአፍታ፡ አንገታችንን ዝቅ እናደርጋለን።

197 አሁንምን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ ይህ የዘወትር ቃልህ ነው። በዚያ ላይ ለሚደረጉ ድርጊቶች ኃላፊነት አልወሰድም፡ እኔ ኃላፊነት የምወሰደው መሰበኬ ብቻ ነው። ይህንን አውቄ (አሁን በጉልምስና-ዕድሜ ያለ ሰው መሆኔን፡ አንድ ቀን በፊትህ እንደምቆም አውቄ)፡ እውነቱን ከልቤ ሰብኬዋለሁ። አንተም ታውቃለህ። ጌታ ሆይ፡ ማንንም ለመጉዳት አይደለም፡ ከሆነ ግን፡ ንስሓ መግባት ያስፈልገኛል።

198 አባት ሆይ፡ አሁን፡ ለታመሙ ጸሎት ሰጀምር፡ እንድትረዳኝ፡ ለጸሎቴን መልሰ እንድትሰጥ እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ ጸሎቴን ብቻ ሳይሆን፡ የዚህች ቤተ ክርሰቲያን ጸሎት፡ የእነዚህ ምስኪኖችም... እዚህ የቆመችው ባለቤቴ ብትሆንስ? ዊልቼር ላይ ያለችው፡ እሷ ብትሆንስ? ወይስ እህቴ? እናቴ? አቤቱ፡ አምላክ ሆይ፡ ህዝቡ ፈውሳቸው። ጌታ ሆይ፡ ትፈውሳቸዋለህን?

199 በጸሎት መሰመር ላይ፡ የልብ ችግር፣ ካንሰር፣ እጢ፣ ሁሉንም አይነት በሽታዎች እና ሰቃዮች፣ ተመልከት። ብዙዎቹ እየመጡ ነው (ጌታ ሆይ፡ መቶዎች፡ እዚህ እየዳኑ ነው)፣ አይተውታል፡ አምነዋል፡ የራሳቸውን ለመቀበል ወደ ጸሎቱ መሰመር እየጎረፉ ናቸው። ወደ ባርያህ ሳይሆን፡ ወደ ህያው ድንጋይ ወደ ልጅህ፡ ወደ ኢየሱስ፡ ወደ ቤተ ክርትያን ራስ፡ በመካከላችን ወዳለው ሰማያዊ አካል፡ ወደ መንፈሳዊው ሰው፡ እየቀረቡ ነው። ሰሙንም እየጠራን፡ ስንሄድ ("በሰሜ አጋንንትን ያወጣሉ።" ብለሃል፡)፡ ጸሎታችንን እንድትመልሰልን፡ በኢየሱስ ሰም እጸልያለሁ። ኣሜን።

200 አሁን፡ ሁሉም ሰው በጸሎት ውሰጥ ይሁን። አሁን፡ ይህ የእናንተም ነው። ጸሎታችሁ ነው።

ይህች ምስኪን ሴት፡ አንድ ነገር ካልረዳት ትሞታለች።

201 ወንድም ሰታድሰክሌቭን የምታውቁት ሰንቶች ናችሁ? ወንድም እና እህት ሰታድሰክሌቭን? በቀደም ማታ፡ ህጻን ልጃቸው ሞቶባቸው ከጀርመን አገር ሶሰት ጊዜ ተደወለልኝ። ጠየቁ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ፡ ሙታንን ሰታሰነሳ አይተናል፡" (ቆመው አይተዋል። አያችሁ? ) "አንተ የጌታ ነብዩ መሆንህን እናውቃለን። ቃል ብቻ ተናገር።"

"እፊ ላይ ካላሰቀመጠልኝ በቀር፡ እኔ ማለት አልችልም፡" አልኳቸው።

"ወደ ጀርመን ና።" ወድያው ተነሳሁ። እና ደወሉልኝ፦ "በሰድሰት ሰዓት ውሰጥ ወደ ጀርመን የሚያደርሰህ የጄት አውሮፕላን ተዘጋጅቷል።" የሞተ

ልጅ ለማስነሣት ወደ ጀርመን የሚበር የጦር ጄት። ከሉዊስቪል እስከ ሙኒክ፡ ጀርመን የጦር ጄት በስድስት ሰዓት ውስጥ ይወስደኛል።

202 ገብቼ ተንበርክክኩና እንዲህ አልኩት። “አባት ሆይ ምን ልበል? በአፌ ተናገር።” አልመለሰልኝም። ወደ ጫካው ወጣሁ፡ “አባት ሆይ ምን ልበል? አልኩት፡ ቃላቶች በአፌ ውስጥ አስቀምጥ። ካልሆነ፡ በከንቱ እሄዳለሁ።” ወደ ኋላ ተመለስኩ፡ አልመለሰልኝም። ገባሁ። ሌሊቱን ሁሉ ጸለይሁ፡ “ጌታ ሆይ፡ ቃላቱን በአፌ ውስጥ አድርግ።” ምንም አልመለሰም።

203 በማግስቱ ጠዋት ባለቤቴ ተነሳች። ልክ እንደወጣች ቃሉ መጣ (ተነሳሁ)፡ “ይህ የጌታ እጅ ነውና። ይህን አትገስጽ አለኝ።” ኽረ-እህ።

ከዚያም በፍጥነት ሰልኩ ደውዬ፡-“መምጣት አልችልም። ኖ፣ ይህ የጌታ እጅ ነው። ተከልክያለሁ።” በዚያ ተግሣጽ ምን ኃይል እንዳለ አይታችኋል? እግዚአብሔር፡- “የጌታ እጅ ነውና ያንን አታድርግ፡” ብሏል።

204 አንድ ጊዜ፡ ሙሴ፡ የሆነ ነገር አታድርግ ተብሎ ነበር፡ እርሱ ግን፡ ሄደና አደረገ። ታስታውሳላችሁ? ስለዚህ እኔ—አልሄድኩም።

205 ከጸሎት እና ከሞት ተግሳጽ በኋላ፡ በዶክተሮች መሞታቸው የተነገረላቸውን፡ አራት የተለያዩ ሰዎችን ለማሳየት፡ መግለጫዎችን ላመጣላችሁ እችላለሁ። አያችሁ? ያንን ነገር ለመገሰጽ በዚያ እንቆማለን። እግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ ኃይል ከሰጣችሁ፡ ስለምታደርጉት ነገር ጥንቃቄ አድርጉ። አያችሁ? “አታድርግ… ” ሲል፡ ብትጠነቀቁ ይሻላል-…

206 እንግዲህ፡ አስታውሱ፡ ምናልባት ለእናንተ ትንሽ ነገር ሊመስላችሁ ይችላል፡ ለእኔ ግን፡ ትርጉም አለው። አያችሁ?

(ስድስት-ተኩል አካባቢ፡ ይመስለኛል፡ ከማለዳው ስድስት-ተኩል ነበር) እጅግ የሚጣፍጥ፡ ትሁት ድምጽ “ይህን አትገስጽ።” “ይህ የጌታ እጅ ነው። አትገስጸው፡” አለኝ።

እኔም “ተመስገን፡ አባቴ። አመስግንሃለሁ፡ ጌታዬ። አላደርገውም፡” አልኩት።

207 “ሾልኮ የገባ ጠላት ነው፡ ገስጸው።” ቢለኝ ኖሮ።

“እንሂድ፡” እላቸው ነበር። በተፈጸመም ነበር።

208 ፊንላንዳዊው ህጻን ልጅ በዚያ ወድቆ፣ ሞቶ፣ ተጋግጦ፣ በሰውነቱ ውስጥ ጤናማ አጥንት እንኳ አልቀረም ነበር፣ ጌታ ግን ይህ የሰይጣን እጅ ነውና፡ “ገስጸው፡” አለኝ።

209 እኔም “ሞት ሆይ፡ እሱን መያዝ አትችልምና። መልሰው፡ ይፈታ፡” አልኩት። ወዲያውም፡ ዘሎ ተነሳና፡ አንድም አጥንቱ፡ ከሰውነቱ አልተሰበረችም። ያ የጌታ ቃል ነው። የጌታ ቃል ወደ እኔ እስኪመጣ ድረስ የጌታን ቃል መጠቀም አልችልም።

210 ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣ የጌታ ቃል ለበሽተኞች እንድጸልይ ተልእኮ ሰጥቶኛል፤ እንድትጸልዩላቸው ተልእኮ ለእናንተም ሰጧችኋል። አሁን፡ “የእምነት ጸሎት ድውያንን ያድናል፡” ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ እንጸልይ፡ እናንተ ቀጥሉና፡ እሱ የሚለውን እናያለን።

211 ክርስትያን ነሽ፡ አይደል? ኢየሱስ ሊያድንሽ እንደሆነ በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? እህቴ፡ ለብዙ ዓመታት ትንሽ የሆድ ህመም፡ አስቃይቶሻል። አሁን፡ ካመንሽ፡ ትፈወሻለሽ።

212 አሁን፣ ጌታ አምላክ ሆይ፣ ይህችን ወጣት ካልረዳሃት በቀር ትሞታለች። አሁን እያየኋት፡ እጸልያለሁ፡ የምትሞትበት ምንም ምክንያት አይታየኝም።

አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ በመንፈሴ ውስጥ፡ ይህን እንድገስጽ፡ ይሰማኛል፤ አንተ ሰይጣን ልቀቃት!

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ትፈወስ፡ ወደዚች ቤተ ክርስቲያን መጥታ ስለ እግዚአብሔርን ክብር ትመስክር። ኣሜን።

213 አሁን፣ ልክ እንደዚች፡ እመቤት፡ አንተም ትድናለህ። አንተ ወንድም ታምናለህ?

እዚህ ደህና እንደምትሆን፡ ታምናለህ? አሁኑኑ ሂድና፡ የፈለግከውን መብላት ጀምር... ከዚያ ደህና ትሆናለህ።

ከእንግዲህ፡ ሸባ ልታደርግህ፡ በስትሮክ የመታችህን ዓለም፡ ሸባ እንድታደረጋት፡ ስትሮኳን እንድትሰጣት ይጠበቅብሃል። አሁን፡ የኃጢያት ስርየትን ለመሰጠት ስትሮክን ከአለም የሚያነሳ የሰማይ አምላክ፣ ስትሮኩን ከላያችሁ ወስዶ፡ ያዳናችሁ፡ በዚያው ስም፡ የኃጢአትን ስርየት ሊሰጣችሁ ይችላል።

የልብ ምትህን እንደሚፈውስ ታምናለህ? ታምናለህ፡ ትፈወሳለህ... ? ...

214 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ይህች ምስኪን ሴት ቀሪ ህይወቷን በዚህ ወንበር ላይ ተቀምጣ ልትሞት ትችላለች። እኛ ግን ይህ የሰይጣን ኃይል ከእርሷ እንዲወሰድ እየጠየቅን ነው። በህይወት ትኑር ትራመድ እንደ ቀድሞ ህይወቷ ትሁን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

215 ታምኛለሽ? ያለቀለት ስራ ነው፡ ተከናውኗል። ምንድን ነው ችግሩ? ያለ ፍርሃት፡ ያለ ምንም... ነገር... ? አንድ ጊዜ ከካንሰር ተፈውሰሻል... ? ... ተፈቺ፡ ሁሉንም ነገር ለኢየሱስ ሰጪው።

216 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በዚህች ሴት ላይ እጄን ጭኜ ሕመሟን ገሥጻለሁ። በመንፈስ የተወለደች፡ ክርስቲያን መሆኗን አውቃለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ ስም፡ ከእርሷ አነሳዋለሁ። ኣሜን።

217 ጌታ አምላክ ሆይ፣ ስለ ውድ ወንድሟ፣ መዳኑን በኢየሱስ ስም እለምናለሁ። በዚያ ላይ ይጽና። ኣሜን። ይሆናል።

218 ልጄ ሆይ ፈውስህን ለመቀበል ተዘጋጅተሃል? እሺ፡ ወደ እጁ ወስዶታል።

219 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ካንተ ዘንድ፡ ፈውሱን ለማግኘት፡ በሚጸልየው፡ በዚህ ወጣት ላይ። እንደ አገልጋይህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጄን በእርሱ ላይ እጭናለሁ... ? ... ኣሜን።

አሁን፡ ማናችሁም... ? ... ይሁን ሰሙን ብቻ ትጠራላችሁ። ወደ—እኔ፡ አይደለም።... ? ...

220 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ልጅ አንዱ በእናቱ እቅፍ እንደሚደገፍ፡ እሷም አሻሽታው—አብራው ትጸልያለች ዳዴ በሚልበት ወቅትም ትንሿ

እጁን ትይዛለች። አሁንም፡ ሰይጣን ይህችን ሴት ወደ አእምሮ በሽተኞች ተቋም ውስጥ አስገብቷታል። እግዚአብሔር፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ተወለደች፣ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ቅድስት ቤተክርስቲያን፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደሚያድርባት ቤተ ክርስትያን ይመጣል፡ እራሱንም ይገልጣል። ዛሬም በጸሎት፡ ያቺን ሴት፡ ከዚያ ተቋም ነፃ አወጣናት። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንጸልያለን። ኣሜን።

ተፈውሰሻል፡ ወደ ቤት ሂጂ።

ለእናትህ እየጸለይሽ፡ ስለመጣሽ አመሰግናለሁ፡ ትክክለኛ ልጅ ማለት እንዲህ ነው።

221 ነጻ መውጫ ቀንሽ ዛሬ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ለዚህች ወጣት ሴት፡ ለባልዋ መዳን እና የጉሮሮዋን መፈወስ፡ "መጥተን፡ እንድናምን፡" ከዚያ በኋላ ያለቀለት ጉዳይ እንደሆነ፡ በተናገረው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ትቀበል።

222 ጌታ ሆይ፡ ሐኪሞች፡ ጌታ ሆይ፡ በሰውነቷ ውስጥ ነው፡ ወደ ዐይንዋ እየወጣ ነው ብለዋል። ይህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስትጸልይ፡ በዚህ መሠዊያ ላይ፡ ለመፈወስ መጥታለች፣ ነፃ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጠይቃለሁ፣ ይህ መቅሰፍት ሰውነቷን ይልቀቅ። ያለቀለት ስራ ነውና።

ለልጇ፡ ይህን መሀረብ እባርከዋለሁ። ጤነኛ ሁኔታ ይመለስለት ጆሮው እንደገና መስማት ይጀምር... ? ...

223 አሁን ቤተክርስቲያን ትናገራለች፡ ቤተክርስቲያን ምስጢራዊ የክርስቶስ አካል ነች። ሁላችንም እንጸልይልሻለን። እያችሁ? ከእንግዲህ—በዓለም እንደሆንን አንልም። የምንናገረው ወዴት እንደምንሄድ እያሰብን አይደለም። መንገዱን አግኝተናል። የተወለድነው በዚያ መንገድ ነው። የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነን (አካሉ ነን)፡ እርግጥ ነው፡ በመላው ዓለም ተበታትነናል። ዛሬ ይህ ቡድን ግን ከእነሱ አንዱ ነው። ዛሬ አብረን በስሙ መጥተናል። አድርጉ ያለንን እናደርግ ዘንድ፡ መጣን። አብረን ስንሆን የማይገልጠው ምን አለ። ለታመሙ ሰዎች ጸልዩ፡ እጃችሁን ጫኑባቸው፡ "የእምነት ጸሎት ድውያንን ታድናለች።"

224 የልብ ችግር ይልቀቅሽ። እግዚአብሔር ለሰጠኝ ተልዕኮ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እታዘዛለሁ... ? ...

**ያን ቀን በቀራንዮ** AMH60-0925

(That Day On Calvary)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ጠዋት፡ መስከረም 25፡ 1960፡ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ U.S.A. ከሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org